# የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት (አፋሕድ)

# AMHARA FANO PEOPLE'S ORGANIZATION (AFPO)

# ፍኖተ-መርህ

# MANIFESTO

## አፋሕድ

የአማራን ሕዝብ የኅልውና አደጋ ይቀለብሳል፤

ዘላቂ ሰላምና ፍትሕን ያሰፍናል!

## AFPO

Reverses the existential threat to the Amhara people, and
Establishes lasting peace and justice!

መስከረም፣ ፳፻፲፰ ዓ.ም

## መቅድም

የአማራ ሕዝብ ላለፉት ሃምሣ ዓመታት በተከታታይ በነበሩ ሥርዓቶች የዘር ማጥፋት ወንጀል የተፈጸመበት፣ እኩልነትን የተነፈገ፣ ፍትሕን ያጣ፣ ማኅበራዊና ታሪካዊ መሠረቱ እንዲናጋ የተደረገ እና ጥያቄውን በተደራጀ መልኩ እንዳያቀርብ ሕገ-መንግሥታዊና ፖለቲካዊ መገለል የደረሰበት ሕዝብ ነው። “ወርቅ ላበደረ ጠጠር” እንዲሉ እንደ ሕዝብ ለሀገር ያበረከተውና የከፈለው ዋጋ በአሉታዊ መንገድ ተተርጉሞ በሃሰት ትርክት በተሠራ የፖለቲካ ስብከት በሄደበት ሁሉ መዋቅራዊና መንግሥት መር በሆነ መንገድ ለጥቃት እንዲጋለጥ እና ኅልውናው አደጋ ውስጥ እንዲወድቅ ተደርጓል።

ስለሆነም ይህ የትጥቅ ትግል እጅግ ውስብስብ በሆነ መንገድ ጨፍጫፊውና ፋሽስቱ የብልጽግና ሥርዓት በአማራ ላይ አቅዶ እየፈጸመ ያለውን የዘር ማጥፋት ዘመቻ ለመቀልበስ የተጀመረ ሕዝባዊ ትግል ነው። የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት ዋና ግቡም በአማራ ላይ ያንዣበበውን የጥፋት ደመና በአስተማማኝ ደረጃ መቀልበስና ሕልውናውን በዘላቂነት ማስቀጠል ነው።

አማራው ያጋጠመውን ምስቅልቅል ችግር ለመፍታት ወደ ትግል ገባ እንጂ ለደረሰበት ግፍና በደል ማንኛውንም ማኅበረሰብ ተጠያቂ አያደርግም። በጠላትነትም አይፈርጅም። ይልቁንም ልክ እንደ አማራው በማናቸውም ምክንያት ግፍና ጭቆና ከሚደርስባቸው እና የመጨፍለቅ አደጋ ከተጋረጠባቸው ሌሎች ነገዶች ጋር በትብብር የሚሠራ ይሆናል። ጥቂት ጽንፈኛና ግራ ዘመም የፖለቲካ ኃይሎች የፈጠሩትን የስህተት መንገድ በማረም በዕውነትና በቁርጠኝነት ከሁሉም የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋር በጋራ እጣፈንታችን ዙሪያ በትብብር ለመሥራት ሁሌም ዝግጁ መሆናችንን መጠቆም እንፈልጋለን።

## Preamble

The Amhara people have been subjected to continuous ethnic cleansing, denial of equality, injustice, and disruption of their social and historical foundations over the past fifty years under successive regimes. They have also faced constitutional and political marginalization, preventing them from formally presenting their demands. Despite their significant contributions and sacrifices to the nation, their value has been negatively interpreted, twisted by false narratives, and weaponized through political rhetoric, making them vulnerable to structural and state-led attacks, pushing them to the brink of annihilation.

Therefore, this armed struggle is a complex, people’s movement initiated to counter the genocidal campaign that the murderous and fascist Prosperity regime has planned and is executing against the Amhara people. The main goal of the Amhara Fano People’s Organization is to decisively reverse the looming cloud of destruction over the Amhara people and to sustainably ensure their existence.

While the Amhara people entered this struggle to resolve their chaotic situation, they do not hold any community accountable for the injustices and oppression they have suffered. Nor do they consider anyone an enemy. Instead, they will work in solidarity with other oppressed peoples who face similar injustices, oppression, and threats of annihilation. We want to emphasize our continuous readiness to work together with all segments of society, in truth and with commitment, on issues concerning our shared destiny.

AMHARA FANO PEOPLE'S ORGANIZATION

## ማውጫ

መቅድም i
መግቢያ 1
ምዕራፍ አንድ 4
የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት የትጥቅ ትግል መነሻ ምክንያቶች፣ ድርጅታዊ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ እና ግቦች 4
1.1 የትግል መነሻዎች 4
1.1.1 በአማራ ሕዝብ ላይ የዘር ማጥፋት፣ በሰብዓዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች እንዲሁም ለኅልውና አደጋ መጋለጡ 4
1.1.2 የፖለቲካ ክህደት 6
1.1.3 ለአማራ ሕዝብ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ አለመስጠት 7
1.1.4. በአማራው ላይ ጥላቻ፣ የተሳሳቱ ትርክቶች እና ጥቃትን የሚያነሳሱ የመንግሥት ፖሊሲዎች 8
1.1.5. የአማራ ማኅበረሰብ ከልማት ተጠቃሚነት ስልታዊ በሆነ መልኩ እንደገለልና ለከፍተኛ ችግር እንዲጋለጥ መደረጉ 9
1.2 ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ፣ ርዕዮተ-ዓለም 9
1.3 የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት የትግል ግቦች 10
ምዕራፍ ሁለት 21
የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት ቁልፍ መርሆዎች 21
2.1 የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት 21
2.2 እኩልነትና ነፃነት 21
2.3 የሃይማኖትና የመንግሥት መለያየት 21
2.4 በትብብር መሥራት 21
2.5 የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን ማክበር 22
ምዕራፍ ሦስት 23
የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት ፕሮግራሞች 23
3.1የፖለቲካ ፕሮግራም 23
3.1.1 ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና የሰብዓዊ መብቶች መከበር 23
3.1.2 የመንግሥት ስልጣን አወቃቀር 24
3.1.3 የውጭ ግንኙነት 26
3.1.4 የሽግግር ጊዜ 26
3.2 የኢኮኖሚና የዕድገት ፕሮግራሞች 27
3.2.1. የሰው ሀብት ልማት 27
3.2.2 የመሬት ባለቤትነት 29
3.2.3 ግብርና 30
3.2.4 ኢንዱስትሪ 30
3.2.5 ንግድ 30
3.2.6 መሠረተ ልማቶች 31
3.2.7 የቱሪዝም ሃብት 31
3.3 ማኅበራዊ ፕሮግራሞ 31
3.3.1 ትምህርት 31
3.3.2 ጤና 32
3.3.3 ባህል 33
3.3.4 ሚዲያ 33

## Contents

Preamble ii
Introduction 1
Chapter One 4
The Genesis and Goals of the AFPO's Armed Struggle, Vision, Mission, Aims and Goals 4
1.1 Genesis of the Struggle 4
1.1.1 Genocide, Human Rights Violations, and the Existential Threat Facing the Amhara People 4
1.1.2 Political Betrayal 6
1.1.3 Failure to Address the Demands of the Amhara People 7
1.1.4. Government Policies Inciting Hatred, Misleading Narratives and Attacks against the Amhara 8
1.1.5. Systematic Exclusion of the Amhara from Development and Exposure to Hardship 9
1.2. Vision, Mission, Objectives and Ideology of AFPO 9
1.3 Goals of the Amhara Fano People’s Organization's Struggle 10
Chapter Two 21
Key Principles of the Amhara Fano People’s Organization 21
2.1 Territorial Integrity and Sovereignty 21
2.2 Equality and Freedom 21
2.3 Separation of Religion and State 21
2.4 Working in Collaboration 21
2.5 Respect for Human Rights Conventions 22
Chapter Three 23
Amhara Fano People’s Organization Programs 23
3.1 Political Programs 23
3.1.1 Building a Democratic System and Respect for Human Rights 23
3.1.2 Government Structure 24
3.1.3 Foreign Relations 26
3.1.4 Transitional Period 26
3.2 Economic Programs 27
3.2.1. Human Resources Development 27
3.2.2 Land Ownership 29
3.2.3 Agriculture 30
3.2.4 Industry 30
3.2.5 Trade 30
3.2.6 Infrastructure 31
3.2.7 Tourism Resources 31
3.3 Social Programs 31
3.3.1 Education 31
3.3.2 Health 32
3.3.3 Culture 33
3.3.4 Media 33

## መግቢያ

የአማራ ሕዝብ ከዳማት (ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ8ኛው እስከ 4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ ሥርዎ መንግሥት) ጀምሮ እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን የዘለቀ የሀገረ መንግሥት ግንባታና ጥልቅ ታሪክ ያለው ሕዝብ ነው። ከሌሎች ወንድምና እህት ኢትዮጵያዊያን ጋር ሆኖ የአማራ ሕዝብ ከሺህ ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ታሪክ፣ ገናና የግዛት አንድነትና ትልቅ ሀገር መፍጠር የቻለ፤ በዓለም ላይ ጉልህ ከሚባሉ የግሪክ፣ የሮም፣ ፋርስና የቻይና ስልጣኔዎች የሚስተካከል ታሪክ ባለቤት ነው።

ጥንታዊና ታሪካዊ ሀውልቶች፣ የላሊበላ ውቅር አብያተ-ክርስትያናት፣ የጣና ጥንታዊ ገዳማት፣ የጎንደር ቤተ-መንግሥት ወዘተ የአማራ ሕዝብ ቀደምት ስልጣኔ ባለቤት መሆኑ ቋሚ ምሥክሮች ናቸው። በተለይም በመካከለኛው ዘመን በአፄ አምደ-ጽዮንና አፄ ዘርዓያቆብ ዘመነ መንግሥት የአማራው ፍፁም የከፍታ ዘመን የነበረ ሲሆን በሥነ-ጽሑፍ፣ በሥነ-ፈለክ፣ በወታደራዊ ሳይንስ፣ በአስተዳደር ጥበብና በሌሎችም ዘርፎች ከፍተኛ እምርታ የታየበት ወቅት ነበር።

የአማራ ሕዝብ በሥነ-ህንፃ፣ በዘመን አቆጣጠር፣ በሥነ-መንግሥት፣ በኪነ-ጥበብ ለተከታታይ ሺህ ዘመናት የዳበረ ሥልጣኔ ባለቤት ቢሆንም ሂደቱ ግን አልጋ በአልጋ አልነበረም። ይልቁንስ ከውጭ እና ከውስጥ ከሚነሱ ጠላቶች በቀጥታና በተዘዋዋሪ ከፍተኛ ጥቃት እየደረሰበት ነበር። ኦቶማን ቱርክ፣ ግብፅ፣ ሱዳን፣ እንግሊዝ፣ ጣሊያንና በእነዚህ ሀገራት በሚታገዙት የሀገር ውስጥ የጎሳ አክራሪና የኃይማኖት ጽንፈኞች ምክንያት መጠነ-ሰፊ ውድመት ደርሶበታል። ይሁን እንጅ የአማራ ሕዝብ ራሱን በብቃት በመከላከል ኅልውናውን በዘላቂነት ማስጠበቅ ችሏል።

የአማራ ሕዝብ የተለያዩ የኢትዮጵያ ነገዶች ሲያደርጉት የነበረውን የማያቋርጥ የእርስ በእርስ ጦርነት (ይህ በአንድ

## Introduction

The Amhara people have a deep history of state-building that spans from Damat (the kingdom that riened from 8$^{th}$ -4$^{th}$ century BC) up to the 20th century. Together with other brother and sister Ethiopians, the Amhara people have a history spanning over a thousand years, having created a glorious territorial unity and a great nation; they possess a history comparable to the prominent Greek, Roman, Persian, and Chinese civilizations.

Ancient and historical monuments, the rock-hewn churches of Lalibela, the ancient monasteries of Tana, the castles of Gondar, etc., are permanent witnesses to the Amhara people's early civilization. Particularly during the Middle Ages, the reigns of Emperor Amde Tsion and Emperor Zera Yaqob marked a golden age for the Amhara, a period that saw significant advancements in literature, astronomy, military science, administrative art, and other fields.

Although the Amhara people have possessed a developed civilization in architecture, calendar systems, statecraft, and art for successive millennia, the process was not without challenges. Instead, they faced severe direct and indirect attacks from external and internal enemies. The Ottoman Turks, Egypt, Sudan, England, Italy, and local ethnic extremists and religious fundamentalists supported by these countries caused extensive destruction. Nevertheless, the Amhara people successfully defended themselves and permanently secured their existence.

The Amhara people were able to halt the continuous internal conflicts waged by various Ethiopian tribes (this includes wars fought between different clans

ብሔር ውስጥ ጭምር በተለያዩ ጎሳዎች መካከል ሲደረግ የነበረውን ጦርነት ይጨምራል ምሳሌ፡- በኦሮሞ ጎሳዎች መካከል ሲደረጉ የነበሩ ጦርነቶችን) በማስቆም እና ጠንካራ ሃገረ-መንግሥት መመሥረት የቻለ ነው። ወራሪዎችንና ቅኝ ገዥዎችን በማሳፈር በአፍሪካ ብቸኛዋን ነፃ ሀገር ሆና የፓን አፍሪካን እሳቤዎች ያዋለደች እና በመላው ዓለም በቅኝ ግዛት ሥር ሲባዝኑ ለነበሩ የዓለም ሕዝቦች ተስፋ እና ምልክት የሆነች ሀገር መገንባት ችሏል። ለመላው ጥቁር ሕዝብ የነፃነት አርማ የሆነችው ሀገራችን ኢትዮጵያ የፓን አፍሪካኒዝም አቀንቃኝና መሥራች በመሆን ሠንደቅ ዓላማዋን ምሳሌ በማድረግ ከጋና እስከ ማሊ፣ ከዚምባብዌ እስከ ሴኔጋል፣ ከአፍሪካ እስከ ካረቢያን ደሴቶች ባሉ ጥቁር ሕዝቦች ሁሉ በተለያየ አሠማመር በመጠቀም የነፃነትና የፓን አፍሪካ ንቅናቄ ማዕከል እንድትሆን አማራ የአንበሳውን ሚና ተጫውቷል። በእጅጉ የሚያሳፍረው የነፃነትና የአንድነት አርማ የሆነውንና ከሀገራችን ሕዝብ አልፎ ለሌሎች ኩራት የሆነውን ሠንደቅ ዓላማ በሀገራችን ማውለብለብ በአብይ መራሹ ጨፍጫፊ ሥርዓት ያለፍርድ ለእሥር እና ለግድያ የሚያበቃ እየሆነ ይገኛል።

ፓን አፍሪካኒዝምን በፓን አፋሪካ የትውልድ ሀገር ለመቅበር ሲባል የፓን አረብ እና መሰል ሠንደቅ ዓላማዎች የተለያየ ስያሜ እየተሰጣቸው በአዲስ አበባችን እና በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች ከፍ ብለው የሚውለበለቡበት ትርክቶች፣ የሕግ ማዕቀፍ እና መዋቅር ሥራ ላይ ውሏል። ይህ በፓን አፍሪካኒዝም የትግል ዕድገት ሂደት ውስጥ ያጋጣመ ትልቅ ስብራት /Setback/ ሲሆን የክፍለ ዘመኑ ታላቅ ቅልበሳ /The great reversal of the Century/ ተደርጎ ሊቆጠር የሚችል ነው። ስለዚህ በአማራ ሕዝብ ላይ የተደቀነውን የኅልውና አደጋ መቀልበስ እና ከአማራ ሕዝብ ትግል ጎን መቆም፣ የአንድ ኩሩ አፍሪካዊ ሕዝብ ኅልውናን ከማረጋገጥም ባሻገር፣ ፓን አፍሪካኒዝምን የመከላከል እና አንድ ደረጃ ከፍ የማድረግ ውጤት ያለው በመሆኑ ነፃነት እና እኩልነት ወዳድ የሆነ መላው የዓለም

even within a single ethnic group, for example, the wars fought between Oromo clans) and establish a strong nation-state. By defeating invaders and colonizers, they built Ethiopia, the only free country in Africa, which gave birth to Pan-African ideas and became a beacon of hope and a symbol for oppressed peoples around the world who were suffering under colonialism. The Amhara played a lion's share in making our country Ethiopia, the emblem of freedom for all black peoples, a proponent and founder of Pan-Africanism, and a center for freedom and Pan-African movements, with its flag serving as an example, used in various ways by black peoples from Ghana to Mali, from Zimbabwe to Senegal, from Africa to the Caribbean islands. It is highly shameful that flying this flag, which is a symbol of freedom and unity, and a source of pride not only for the people of our country but also for others, is now leading to imprisonment and killing without trial under Abiy's brutal regime.

To bury Pan-Africanism in its birthplace, narratives, legal frameworks, and structures have been put in place to allow Pan-Arab and similar flags, under various names, to fly high in our Addis Ababa and in various parts of our country. This is a major setback in the struggle for Pan-Africanism and can be considered 'The Great Reversal of the Century.' Therefore, reversing the existential threat posed to the Amhara people and standing by the Amhara people's struggle not only ensures the existence of a proud African people but also has the effect of defending and elevating Pan-Africanism. This is a truth that all freedom and equality-loving people around the world should support.

ሕዝብ ሊደግፈው የሚገባ ሀቅ ነው። ከታጠቀ ሕዝባዊ አመፅ ተነስቶ ወደ ድርጅት - መር የትጥቅ ትግል የደረሰው ይህ የኅልውና ትግል የተነሳበትን ዓላማ የሚያሳካ የትግል ፕሮግራም መቅረጽ ለነገ የማይባል ሥራ በመሆኑ፣ የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት (አሕፋድ) ይህን የፖለቲካ ፕሮግራም እና የትግል ፍኖተ - መርህ ይፋ አድርጓል።

Since formulating a program of struggle that achieves the goals of this existential struggle, which arose from an armed popular uprising and escalated into an organized armed struggle, is a task that cannot wait, the Amhara Fano People’s Organization (AFPO) has unveiled this political program and roadmap for struggle (manifesto).

# ምዕራፍ አንድ

## የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት የትጥቅ ትግል መነሻ ምክንያቶች፣ ድርጅታዊ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ እና ግቦች

### 1.1 የትግል መነሻዎች

የአማራ ሕዝብ ለኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታና ለሀገር ኅልውና መጠበቅ የተጫወተው ሚና እንደ ወንጀል ተቆጥሮበት ታሪኩ፣ ባህሉና ዕሴቱ እንዲጠለሽ፤ እንዲሁም በሌሎች የኢትዮጵያ ነገዶች እንዲጠላ ፀረ አማራ ትርክት ተፈጥሮ በስፋት ተሠርቶበታል።

በዚህም የተነሳ የአማራ ሕዝብ በትርክት፣ በሕግ እና በሥርዓት የታገዘ መጠነ ሰፊ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈፅሞበታል፤ እየተፈጸመበትም ይገኛል። በተለይም ኢሕአዴግ እንደ ሥርዓት ወደ ስልጣን ከመጣበት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በአማራ ሕዝብ ላይ የሚያደርሰው የዘር ማጥፋት ወንጀል በፍኖተ - መርህ (በማኒፌስቶ) የተጠነሰሰ፣ መንግሥት መርና መዋቅራዊ በመሆኑ አድማሱን አስፍቶ ለሦስት አሥርት - ዓመታት በሰቆቃ እንዲዘልቅ አድርጎታል። በ2010 ዓ.ም የኢሕአዴግ ሥርዓት ወደ ኦሕዴድ መራሹ የብልጽግና አገዛዝ የተቀየረ ቢሆንም ፍትሕና ሰላም አገኛለሁ ብሎ የአማራ ሕዝብ በጉጉት የጠበቀው የኦሕዴድ ብልጽግና ሥርዓት ከልጅነቱ በጥላቻ ተኮትኩቶ ያደገ በመሆኑ የአባቱን ውርሥ ተቀብሎ ለአማራ ሕዝብ ከድጡ ወደ ማጡ ሆኖ ይፋዊ የዘር ማጥፋት ጦርነት ዘመቻ አውጆበታል። በአጠቃላይ የአማራ ፋኖ ወደ ትጥቅ ትግል እንዲገባ ያስገደዱት ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

#### 1.1.1 በአማራ ሕዝብ ላይ የዘር ማጥፋት፣ በሰብዓዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች እንዲሁም ለኅልውና አደጋ መጋለጡ

የአማራ ሕዝብ በዘመነ ኢሕአዴግ በበደኖ፣ በአርባ ጉጉ፣ በወተር፣ በጅማ፣ በወለጋ፣ በመተከል፣ በወልቃይት፣

# Chapter One

## The Genesis of the AFPO's Armed Struggle, Vision, Mission, Aims and Goals

### 1.1 Genesis of the Struggle

The role the Amhara people played in the formation of the Ethiopian state and the preservation of its existence has been deemed a crime. Their history, culture, and values have been distorted and widely used to create anti-Amhara narratives to incite hatred among other Ethiopian peoples.

Consequently, the Amhara people have been subjected to, and continue to be subjected to, extensive ethnic cleansing supported by narratives, laws, and systems. Specifically, since the TPLF-led EPRDF regime came to power in 1991, the genocidal crime against the Amhara people was conceived in a manifesto, expanded in scope, and prolonged for three decades of suffering due to its state-led and structural nature. Although the EPRDF regime transformed into the ODP-led Prosperity regime in 2018, the Amhara people, who had eagerly anticipated justice and peace, found that the ODP Prosperity regime, having been nurtured in hatred from its inception, inherited its predecessor's legacy, plunging the Amhara people from bad to worse by officially declaring a genocidal war against them. The main reasons that forced the Amhara Fano to engage in armed struggle are as follows:

#### 1.1.1 Genocide, Human Rights Violations, and the Existential Threat Facing the Amhara People

During the EPRDF era, the Amhara people experienced massacres in Bedeno, Arba Gugu, Weter, Jimma, Wollega, Metekel,

በጠለምት፣ በራያ፣ በደራ እንዲሁም በሌሎች የሀገራችን ክፍሎች ከፍተኛ እልቂትን አስተናግዷል። በሕዝባችን ላይ የሚፈፀመውን እልቂት ለመታደግ አማራ ብርቱ ዋጋ ከፍሎ አገዛዙን መቀየር ቢችልም ከኢሕአዴግ አብራክ በወጡ ፅንፈኛ የዘውግ ብሔርተኞች ለውጡን በመጥለፍና ራሳቸውን ብልጽግና ብለው በማደራጀት ለኢትዮጵያዊያን በተለይም ለአማራ ሕዝብ የባሰ የጭቆና ሥርዓት እንዲወለድና የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዲቀጥል አድርገዋል።

የኦሕዴድ ብልጽግና ሥርዓት የጅምላ ግድያ አድማሱን አስፍቶ በሻሸመኔ፣ በጅማ፣ በወለጋ፣ በአርሲ፣ በመተከል፣ በሸዋና በሌሎችም አካባቢዎች ከፍተኛ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈጽሟል፣ አሁንም እየተፈጸመ ይገኛል። በተለይም ከፍተኛው የአማራ ጭፍጨፋ የሚፈጸመው በዋናነት የአገዛዙ ቁንጮ አመራሮች በወጡበት የ”ኦሮሚያ" “ክልል” መሆኑና ሕዝባችን ለሚያነሳው የኅልውና ጥያቄ የፌዝና ቀልድ ምላሽ መስጠቱ ኦሕዴድ መራሹ የብልጽግና አገዛዝ ለአማራ ሕዝብ መገደልና መሳደድ እንዲሁም ለኢትዮጵያ መፈራረስ ሕጋዊና መዋቅራዊ ድጋፍ እያደረገ ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው።

በአሁኑ ጊዜ ከኦሮሚያ “ክልል” ብቻ ከሞት እያመለጡ፣ ሃብትና ንብረታቸውን ትተው የሚሰደዱት አማራዎች ብዛት በሚሊዮኖች የሚቆጠር ሆኗል። የአማራን ሕዝብ ለማጥፋት ትርክት ተሠርቶበት፣ ዋና አቀንቃኝና አስፈጻሚ ተፈጥሮለት አማራን በአካል፣ በፖለቲካ ተሳትፎ፣ በሥነ-ልቦና፣ በኢኮኖሚ፣ በእሴት፣ በባህል፣ በቋንቋና በኃይማኖት ጭምር የማዳከም ሥራ ተሠርቶበታል፤ አሁንም እየተሠራበት ይገኛል። የዘር ማጥፋት ወንጀሉ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ በተጠናና በተቀናጀ መልኩ ተቋማዊ ጥቃት እየተፈጸመበት መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል።

አገዛዙ የአማራ ሕዝብ መከታ የሆነውን ልዩ ኃይል በተለየ ሁኔታ እንዲፈርስና ትጥቁን እንዲፈታ ካደረገ በኋላም

Welkait, Tselemti, Raya, Derra, and other parts of the country. Despite the Amhara people making immense sacrifices to change the regime and stop the massacres, the change was hijacked by extremist ethnic nationalists who emerged from the EPRDF, forming the Prosperity Party. This led to the birth of an even more oppressive system for Ethiopians, especially the Amhara people, and the continuation of the genocidal crime.

The ODP-led Prosperity regime escalated mass killings in Shashemene, Jimma, Wollega, Arsi, Metekel, Shewa, and other areas, committing and continuing to commit widespread ethnic cleansing. The fact that the largest massacres of Amhara people occur primarily in the "Oromia" region, where the regime's top leaders originate, and that our people's existential questions are met with mockery, confirms that the ODP-led Prosperity regime supports the killing and displacement of Amhara people and the disintegration of Ethiopia through legal and structural means.

Currently, millions of Amhara people are fleeing from the Oromia region alone, escaping death and abandoning their property. The Amhara people have been targeted with narratives aimed at their destruction, with chief instigators and executors created to physically, politically, psychologically, economically, culturally, linguistically, and religiously destroy the Amhara.

This weakening effort has been ongoing and continues today. It has been confirmed that, from the moment the genocide began, institutional attacks have been systematically and continuously carried out against them.

The regime's clear intention was to eliminate the Amhara people from existence, as evidenced by its dismantling

የፋኖንና የአርሶ አደሩን መሣሪያም ለመሰብሰብ ወደ ተግባር የገባው ያለማንም ከልካይ አማራ የሚባልን ሕዝብ ከምድረ-ገጽ ለማጥፋት መሆኑ ግልፅ ነበር።

በኦሮሚያና በአንዳንድ “ክልሎች” ተወስኖ የነበረው የአማራ ጭፍጨፋ አድማሱን አስፍቶ በተቀናጀ የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች “አማራ ክልል” ላይ በሁሉም ዞኖችና ወረዳዎች ትሥሥር(network) በመዘጋት፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማወጅ በድሮንና በሜካናይዝድ ጦር ጭምር እንደ ሕዝብ ለማጥፋት እየተጨፈጨፈ በመሆኑ ራሡን ከእልቂት ለማዳን ወደ ጦርነት ተገዶ እንዲገባ ተደርጓል።

### 1.1.2 የፖለቲካ ክህደት

የአማራ ሕዝብ ከሃምሳ ዓመታት በላይ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ፍትኃዊ ውክልና እና ተሰሚነት አጥቷል። በአማራ ሕዝብ ላይ የሚደርሱ ችግሮች መንግሥት መር በሆነ ሴራ መከናወናቸው፣ አማራው ከፖለቲካ መድረኩ እንደተገለለ ማሳያዎች ናቸው። የፖለቲካ ውሳኔ ሰጪነት ደረጃዎች ላይ ሀቀኛ ተወካዮች አለመኖራቸው እንዲሁም የነበሩትም ቢሆኑ ለሕዝብ ጥቅም የቆሙ ሳይሆኑ ለሥርዓቱ ታማኝና ራስ ወዳድ የሆኑ ካድሬዎች ስልጣን መያዛቸው፣ በአማራው ላይ ለሚደረገው ግፍና በደል ድምጽ ሊሆን የሚችል ውክልና እንኳን እንዳይኖረው ተደርጓል፡፡

ትክክለኛ ውክልና አለመኖር የፖለቲካዊ መገለል አንዱ መገለጫ ሲሆን፣ ለሕዝቡ የኅልውና ስጋትም መንስኤ ሆኗል።

በርካታ የአማራ ወጣቶች በግንባር ቀደምትነት ብርቱ ዋጋ ከፍለው በ2010 ዓ.ም ፖለቲካዊ ለውጥ እንዲመጣ ቢያደርጉም፣ የአማራ ሕዝብ በተከፈለው ዋጋ ልክ ተገቢውንና ፍትሓዊ የሆነ የፖለቲካ ውክልና (ስልጣን) አላገኘም። በተቃራኒው ሃቀኛ የአማራ አመራሮችን በሤራ ከማስገደል ጀምሮ ከፍተኛ የሆነ ፖለቲካዊ ሸፍጥ ተፈጽሞበታል። የአማራ ሕዝብም በየቦታው እንዲገደልና

of the Amhara special forces, disarming them, and then proceeding to collect weapons from Fano and farmers.

The Amhara massacre, which was confined to Oromia and some other regions, has expanded in scope, with the government's security forces besieging all zones and districts in the "Amhara region" through a network. By declaring a state of emergency, using drones and mechanized warfare, the Amhara people are being massacred as an ethnic group, forcing them to engage in war to save themselves from annihilation.

### 1.1.2 Political Betrayal

For over fifty years, the Amhara nation has lacked fair representation and voice in Ethiopian politics.

In particular, both past and present governments have orchestrated problems targeting the Amhara people through government-led conspiracies, which are indications of the Amhara being politically marginalized. Lack of honest representatives at decision-making levels, and the fact that those who were in power were not standing for the public's interest but were rather highly selfish individuals recruited to hold power, has exacerbated political betrayal.

The lack of representation is evident in high-ranking leadership positions within federal government ministries, as well as defense, security, and justice institutions. Consequently, policies reflecting the interests of the Amhara people are not formulated, and grievances and security concerns affecting the community do not receive adequate attention. The absence of representation is a clear manifestation of political marginalization and a source of existential threat to the people.

Although many Amhara youths made significant sacrifices on the front lines, leading to political change in 2018, the

እንዲፈናቀል ተደርጓል። የፌደራል መንግሥቱንና አዲስ አበባንም ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ በኦሕዴድ ብልጽግና ቁጥጥር ሥር እንዲወድቅ ተደርጓል።

### 1.1.3 ለአማራ ሕዝብ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ አለመስጠት

በሀገረ መንግስቱ ግንባታ ላይ ከፍተኛ ሚና የነበረው የአማራ ሕዝብ ለዘመናት በሠላማዊ መንገድ ሲያነሳቸው ለነበሩ ፍትኃዊ ጥያቄዎች መልስ ከመስጠት ይልቅ መንግሥት መር የሆነ ከፍተኛ የኅልውና አደጋ እንዲጋረጥበት እንዲሁም ሀገር አልባ እንዲሆን ተደርጓል። የወሰንና የማንነት ጥያቄዎችን ከህዝቡ ፍላጎት ፍጹም ተቃራኒ በሆነ መልኩ ለፖለቲካ ቁማር መጫዎቻ በማድረግ እንዲሁም ከክልሉ ውጭ የሚኖረው አማራ በተለያየ ሁኔታ ለከፍተኛ እልቂትና ቀውስ እንዲጋለጥ ተደርጓል። ለባለፉት ሃምሳ ዓመታት ኢትዮጵያን ያስተዳደሩ ተከታታይ መንግሥታት፣ የአማራን ሕዝብ ማንነት፣ መሬት እና እኩልነትን የተመለከቱ መሠረታዊ ጥያቄዎችን በተገቢው መንገድ ለመመለስ ፍቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። የአማራ ማንነት በሌሎች "ክልሎች" ውስጥ ተነፍጎ፣ የአማራ መሬቶች በተለያዩ መንገዶች እንዲወረሩ ወይም የአስተዳደር ወሰናቸው እንዲለወጥ ተደርጓል።

አማራው በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች የመኖር፣ የመስራት እና ንብረት የማፍራት መብቱ በተደጋጋሚ ተጥሷል፤ አማራ መሆኑ ወንጀል ሁኖ በየሄደበት ሁሉ እንደ ሁለተኛ ዜጋ እንዲቆጠርም ተደርጓል። መሬት የማንነት እና የኑሮ ዋስትና በመሆኑ፣ የመሬት ወረራ እና የአስተዳደር ወሰን ለውጦች የሕዝቡን የኅልውና ስጋት አባብሰውታል። መንግስታት ለእነዚህ ጥያቄዎች ግልጽ እና ሁሉን አቀፍ ምላሽ ባለመስጠታቸው፣ ሕዝቡ ቅሬታውንና ብሶቱን በተለያዩ ሰላማዊ የተቃውሞ መንገዶች ቢገልጽም ከፍተኛ የመንግስት አካላት ጥያቄውን ተሳልቀውበታል። ይህም የመንግስት መዋቅርን አለመተማመን እና የራስን መብት በራሱ ለማስጠበቅ የጦር መሳርያ እንዲያነሳ

Amhara people were denied for proper and fair political representation (power) commensurate with their sacrifices. On the contrary, a major political deception was committed, starting with the forced removal of honest Amhara leaders through conspiracy. The Amhara people were also subjected to killings and displacement in various places. The federal government and Addis Ababa were completely brought under the control of the ODP-led Prosperity Party.

### 1.1.3 Failure to Address the Demands of the Amhara People

The Amhara people, who played a significant role in the building of the state, instead of receiving answers to their fair questions, which they had peacefully raised for decades, have been subjected to a grave existential threat orchestrated by the government, leading to their statelessness. Border and identity questions have been used as political pawns, completely against the will of the people, and Amharas living outside the region have been exposed to severe massacres and crises in various situations. For the past fifty years, successive governments that ruled Ethiopia have consistently refused to adequately address the fundamental questions concerning Amhara identity, land, and equality. Amhara identity has been denied in other regions, and Amhara lands have been invaded or their administrative boundaries altered in various ways.

The Amhara's right to live, work, and own property in other parts of the country has been repeatedly violated; a situation where they are treated as second-class citizens has become prevalent. Since land is a guarantee of identity and livelihood, land invasions and administrative boundary changes have exacerbated the existential threat to the people. Because governments have failed to provide clear

አስገድዶታል። የአማራ ሕዝብ ለረጅም ጊዜ ሲያነሳቸው የነበሩ ሰባዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ጥያቄዎችን መመለስ የሚችል ሥርዓት አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን የአማራን ህዝብ ወደ አደገኛ ቅርቃር እንዲገባ ተደርጓል።

### 1.1.4. በአማራው ላይ ጥላቻ፣ የተሳሳቱ ትርክቶች እና ጥቃትን የሚያነሳሱ የመንግስት ፖሊሲዎች

ባለፉት ሃምሳ ዓመታት፣ የመንግሥት አካላትና ከመንግሥት ጋር ቅርበት ያላቸው ሚዲያዎች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ በአማራ ሕዝብ ላይ ጥላቻን የሚያነሳሱ፣ የተሳሳቱ ትርክቶችን የሚያሰራጩ ብሎም በቀጥታ ጥቃትን የሚቀሰቅሱ ፖሊሲ እና መመሪያዎችን አውጥተው ተግባራዊ እንዲሆኑ አድርገዋል።

ታሪካዊ ክስተቶችን በማጣመም እና የተሳሳቱ ትርክቶችን በመፍጠር፣ የአማራን የሀገር ባለውለታነት በማዛባት እና ከሌሎች ብሔሮች ጋር የሚያጋጩ ሀሳቦችን በማስተላለፍ የአማራን ሕዝብ ገጽታ አበላሽተዋል። እነዚህ ትርክቶች በተለይም በመንግስት ቁጥጥር ስር ባሉ ወይም በመንግስት ድጋፍ በሚደረግላቸው የመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት ሲተላለፉ፣ የሕዝብን አስተሳሰብ በመመረዝ በአማራ ላይ ለሚፈጸሙ ጥቃቶች ሥነ ልቦናዊ ዝግጅትን ፈጥረዋል። ይህ ደግሞ "በብሔር ብሔረሰቦች" መካከል የነበረውን ግንኙነት በማሻከር ለከፍተኛ ግጭት አጋልጧል።

እነዚህ የሀሰት ትርክቶችና አግላይ የሆኑ አስተዳደራዊ መዋቅሮችና አሰራሮች አማራው ባልተወከለበት የወጣው ሕገ-መንግስት ከለላ እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡ አግላይ ከሆነው ሕገ-መንግስት የሚቀዱት የመንግስት ፖሊሲዎችም በአማራ ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚደግፉ በመሆናቸው ለችግሩ መባባስ አስተዋጽኦ አድርገዋል። የፀጥታ አካላት በወቅቱ

and comprehensive answers to these questions, the people, though expressing their grievances and seeking to uphold their rights through various peaceful protests, have been mocked by high-ranking government officials. This has led to a distrust of the government structure and forced the people to take up arms to protect their rights themselves.

Not only has there been a lack of a system capable of addressing the human, political, economic, and social questions that the Amhara people have long raised, but the Amhara people have also been pushed into a dangerous predicament.

### 1.1.4. Government Policies Inciting Hatred, Misleading Narratives, and Attacks Against the Amhara

Over the past fifty years, government bodies, state-affiliated media, governmental and non-governmental institutions, and individuals have been observed disseminating policies and messages that incite hatred, propagate misleading narratives, and even directly provoke attacks against the Amhara people. Distorted narratives and historical events, by misrepresenting the Amhara's historical contributions to the nation and spreading ideas that pit them against other ethnic groups, have damaged the image of the Amhara people. When these narratives are disseminated, particularly through state-controlled or state-supported media, they poison public opinion and create a psychological readiness for attacks against the Amhara. This, in turn, has strained relations between ethnic groups and exposed them to conflict.

These false narratives and exclusionary administrative structures and practices have been given protection by a constitution that does not represent the Amhara people. Government policies drawn from the exclusionary constitution

ጥቃት አድራሾችን ለፍትሕ አለማቅረባቸው ወይም ለተጎጂዎች ፈጣን ምላሽ አለመስጠታቸው፣ አብዛኛውን ጊዜ ጥቃት አድራሾችን ከቅጣት እንዲያመልጡ መደረጉ መንግስት በግዴለሽነት ያደረገው ሳይሆን ሆን ተብሎ በጥናት የተደረገ መሆኑ በአማራው ዘንድ ተስፋ ቆርጦ ሌላ አማራጭ እንዲፈልግ አስገድዶታል፡፡

### 1.1.5. የአማራ ማሕበረሰብ ከልማት ተጠቃሚነት ስልታዊ በሆነ መልኩ እንዲገለልና ለከፍተኛ ችግር እንዲጋለጥ መደረጉ

በአማራ “ክልል” የሚኖሩ ዜጎች ከመንግሥት የልማት ፕሮግራሞችና ዕድሎች ሆን ተብሎና ስልታዊ በሆነ መንገድ እንዲገለሉ ተደርጓል። ይህ አስተሳሰብ ክልሉ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ አገልግሎቶች፣ በመሠረተ ልማት እና በሌሎች የልማት መስኮች ወደኋላ እንዲቀር የተደረገው በአጋጣሚ ሳይሆን፣ በታቀደ መንገድ እንደሆነ በግልጽ ይታያል። በዚህም ምክንያት ወጣቶች ለሥራ አጥነት፣ ህዝቡን ለመሠረታዊ አገልግሎቶች እጦት ብሎም ለኑሮ ውድነት እንዲጋለጥ ተደርጓል።

የትምህርት፣ ጤና፣ የመንገድና የመብራት አገልግሎቶች እንዲሁም የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ተደራሽ አለመሆን በክልሉ ውስጥ ፍትሓዊነት እንደሌለ የሚያሳዩ ናቸው። ይህም የዜጎችን ምርታማነት በመቀነስ የክልሉን አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ አቅም በማዳከም የአማራ ሕዝብ ለድህነትና ኋላ ቀርነት እንዲጋለጥ አድርጎታል።

## 1.2. ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማና ርዕዮተ-ዓለም

### ራዕይ

የአማራ ሕዝብ ከህልውና ስጋት ተላቆ፣ የፍትህና የእኩልነት ጥያቄዎቹ በዘላቂነት ተመልሰው፤ ነፃነት፣ እኩልነትና ወንድማማችነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን ማየት።

have also contributed to the worsening of the problem by indirectly supporting the attacks on the Amhara people.

The failure of security forces to bring perpetrators to justice in a timely manner or to respond promptly to victims, often providing cover for perpetrators to escape punishment; this was not done by the government carelessly but deliberately and with careful study, forcing the Amhara people to despair and seek other options.

### 1.1.5. Systematic Exclusion of the Amhara from Development and Exposure to Hardship

Citizens of the Amhara region have been deliberately and systematically excluded from development programs and opportunities. This clearly shows that the region has been left behind in terms of economy, social services, infrastructure, and other areas of development in a planned and organized manner. The lack of access to education, health, road and electricity services, as well as clean drinking water, demonstrates the lack of equity in the region.

This has reduced the productivity of citizens and weakened the overall economic potential of the region, leaving the Amhara people vulnerable to poverty and backwardness.

## 1.2. Vision, Mission, Objectives and Ideology of AFPO

### Vision

To envision an Ethiopia where the Amhara people are free from existential threats; where their demands for justice, equality, and freedom are sustainably fulfilled; and where freedom, equality, and brotherhood prevail as guiding national values.

### Mission

✓ To build a capable and well-organized institution dedicated to safeguarding the

### ተልዕኮ

- ✓ የአማራን ሕዝብ ህልውና ለማስጠበቅ የሚተጋ ብቁ እና የተደራጀ የሰው ኃይል ያለው ተቋም መገንባት፣
- ✓ የተደራጀ እና የተቀናጀ የትጥቅ ትግል በማድረግ በአማራ ሕዝብ ላይ ያንዣበበውን የህልውና አደጋ መቀልበስ፣
- ✓ አማራ የተነፈገውን የነጻነት፣ የፍትህ እና የእኩልነት ጥያቄዎች ማስመለስ፣
- ✓ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን እህትና ወንድሞች ጋር በትብብርና በመከባበር ጠንካራ ሀገረመንግስት መገንባት፣

### ዓላማ

የትግላችን ዋነኛ ዓላማ የአማራ ሕዝብ ለአመታት በአምባገነን ሥርዓቶች እየደረሰበት ያለውን መዋቅራዊና ሥርዓታዊ የህልውና አደጋ በማስወገድ የአማራ ሕዝብ ያለ ልዩነት የሚያነሳቸውን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ጥያቄዎች እንዲመለሱ ማድረግና የሀገር ባለቤትነቱን በልኩ የሚያረጋግጥ አካታች ሕዝባዊ መንግስት መገንባት ነው።

### ርዕዮተ-ዓለም

የአማራ ሕዝብ የስልጣኔ ባለቤት እንደመሆኑ መጠን ባህሉን፣ ሃይማኖቱን እና እሴቱን ጠብቆ የዘመናዊው ዓለም ከሚራመድበት ሁለንተናዊ ዕድገት ጋር የሚጣጣም ቅይጥ ርዕዮተ-ዓለም ማራመድ ሲሆን ዝርዝር ጉዳዩ በጥናት ላይ ይገኛል።

## 1.3 የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት የትግል ግቦች

የአማራ ሕዝብ የሚያነሳቸው የዋሉ ያደሩ በርካታ ጥያቄዎች ቢኖሩትም መሠረታዊ የሚባሉት ግን የሚከተሉት ናቸው። በአማራ ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ጭፍጨፋና የዘር መጥፋት አደጋን የመቀልበስ ጥያቄ፣ የሽግግር ፍትሕና ዘላቂ ሰላምን የማግኘት፣ ዕውነተኛና መተማመን ላይ የተደረሰበት ሕገ-መንግሥት፣ ትክክለኛ የሆነ የሕዝብ ቆጠራና ፍትሓዊ የበጀት ጥያቄ፣ የሃሰት ትርክትን ማረም፣ የወሰንና

existence and interests of the Amhara people;

- ✓ To counter and reverse existential threats facing the Amhara people through organized and coordinated resistance;
- ✓ To restore the fundamental rights of freedom, justice, and equality long denied to the Amhara people;
- ✓ To contribute to the establishment of a strong, cooperative, and respectful state founded on mutual trust among all Ethiopians.

### Objectives

The primary objective of our struggle is to eradicate the structural and systemic existential threats faced by the Amhara people under successive authoritarian regimes. We aim to ensure that the political, economic, and social questions raised by the Amhara people are addressed without discrimination, and to build an inclusive, people-centered government that guarantees national ownership and equality.

### Ideology

Recognizing the Amhara people as a foundational pillar of civilization, it is imperative to preserve their culture, faith, and values while embracing a balanced ideology that harmonizes traditional principles with the global developments of the modern world. A more detailed articulation of this ideology is under further study and development.

## 1.3 Goals of the Amhara Fano People's Organization's Struggle

While the Amhara people have many long-standing demands, the fundamental ones are the following: reversing the ongoing massacre and genocide against the Amhara people, achieving transitional justice and lasting peace, establishing a true and trustworthy constitution, ensuring fair population counts and equitable budget allocations, correcting false narratives, resolving border and

የማንነት ጥያቄን በዘላቂነት መመለስ፣ የእኩል ተጠቃሚነትና በፀጋው ልክ የመልማት፣ እንዲሁም ሥርዓታዊ ለውጥና የፖለቲካ ውክልናን ማረጋገጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ስለሆነም የአማራ ሕዝብ የሚያካሂደው የኅልውና ትግል ዋና ግብ ሕገ መንግሥታዊ፣ እንዲሁም ሥርዓታዊ ለውጥና የሽግግር መንግሥት ለውጥ በማምጣት በአማራ ሕዝብ ላይ የተደቀነውን የኅልውና አደጋ በዘላቂነት መቅረፍ እና ለመላው ኢትዮጵያውያን ዋስትና የሚሰጥ ሕገመንግሥታዊ እና ፌደራላዊ አደረጃጀት መትከል ነው።

### 1ኛ. በአማራ ላይ እየተፈፀመ ያለውን ጅምላ ጭፍጨፋና የኅልውና አደጋ መቀልበስ፣

የአማራ ሕዝብ ከትናንቱ የቀጠለ ጭፍጨፋና የዘር ፍጅት እየተካሄደበት ይገኛል። ይህ የተቀነባበረ መንግሥት - መር ጭፍጨፋ በሰላማዊ መንገድ ለመመለስ የተደረጉት ጥረቶች በሙሉ ውጤታማ አልሆኑም። በዚህም የተነሳ የአማራ ሕዝብ ተፈጥሯዊ የመኖር መብቱን ለመከላከልና ራሡን ከእልቂት ለመታደግ የትጥቅ ትግል ጀምሯል። ከዚህ አንፃር የአማራን ሕዝብ ኅልውና ለማስጠበቅ የሚደረገውን የትጥቅ ትግል ከፊት ሆኖ እየመራ በአማራ ሕዝብ ላይ በሰማይና በምድር እየዘነበበት ያለውን ጦርነት እንደአመጣጡ ለመመከት አፋሕድ አልሞ እየሠራ ይገኛል። ከሕዝብ እምቢተኝነት እስከ ተደራጀ የትጥቅ ትግል ያሉትን ሁሉንም አማራጮች በመጠቀም አፋሕድ በአማራ ሕዝብ ላይ የተጋረጠውን የኅልውና አደጋ ለመቀልበስ የጀመረውን ትግል አጠናክሮ ይቀጥላል፣ ወደፊትም በአማራ ሕዝብ ላይ ከሚመጣበት የኅልውና አደጋ ራሱን ለመጠበቅ አፋሕድ የኅልውና ዘብ ሆኖ የሚቆም ይሆናል።

### 2ኛ. የሽግግር ፍትሕና ዘላቂ ሰላም

identity questions permanently, ensuring equitable benefit and development proportionate to their contributions, and achieving systemic change and political representation. Therefore, the main goal of the Amhara Fano People’s Organization’s existential struggle is to bring about constitutional and systemic change and a transitional government, thereby permanently resolving the existential threat to the Amhara people and establishing a constitutional and federal structure that guarantees the rights of all Ethiopians.

### 1st. Reversing the Massacres and Existential Threat Against the Amhara People

The Amhara people continue to face ongoing massacres and ethnic cleansing. All efforts to resolve this orchestrated state-led massacre peacefully have been unsuccessful. As a result, the Amhara people have launched an armed struggle to defend their inherent right to existence and save themselves from annihilation. In this regard, AFPO is working to counter the war being waged against the Amhara people from all directions, leading the armed struggle to secure the Amhara people's existence. AFPO will strengthen the struggle it has started to reverse the existential threat looming over the Amhara people, utilizing all available options, including popular resistance and organized armed struggle. In the future, AFPO will continue to stand as a guardian of the Amhara people's

የአማራ ሕዝብ ከሰማይ በታች ያሉ አረመኔያዊ ድርጊቶች ሁሉ ተፈፅመውበታል። አማራነት እንደ ጥፋት ተቆጥሮ በሀገሪቱ በሚገኙ በግልፅ በሚታወቁ እና በማይታወቁ እሥር ቤቶች በመንገላታት ላይ የሚገኙ ንጹሃን አማራዎች በአስቸኳይ እንዲፈቱ፤ እንዲሁም እነሱ እና ካሁን በፊት በተመሳሳይ ሁኔታ ያለጥፋታቸው ታሥረው የተንገላቱ አካላት ሁሉ ፍትሕ እንዲያገኙ ማስቻል አንዱ የትግላችን ግብ ነው።

በጨፍጫፊው ብልፅግና እና በግብረ-አበሮቹ ሤራ አማካኝነት ከደንቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ታግተው ደብዛቸው የጠፉ 17 ሴት ተማሪዎችን ጨምሮ በተለያዩ ጊዜያት የተሰወሩ አማሮች ዕጣ ፈንታቸው ተጣርቶ፤ በሕይወት ካሉ ከቤተሰቦቻቸው እንዲገናኙ፤ በሕይወት ከሌሉም ቤተሰቦቻቸው በአግባቡ እንዲረዱ እና ፍትሓዊ ካሣ እንዲያገኙ፣ ወንጀለኞችም ለፍርድ እንዲቀርቡ ይደረጋል። በተደጋጋሚ በአማራ ሕዝብ ላይ ለተደረጉት ሕገ-ወጥ ወታደራዊ ዘመቻዎች እና በዘመቻዎቹ ለጠፋው የሰው ሕይወት፣ ለወደመ ንብረት፣ እንዲሁም በዚያ ምክንያት ለተጎዳው ኢኮኖሚ፣ ለተስተጓጎሉ የትምህርት አና የጤና አገልግሎቶች፣ በእነዚህም ምክንያት ለመከኑ ዕድሎች ሕዝቡና ተጎጂ ቤተሰቦችም ተገቢ ካሣ እንዲከፈላቸው ማድረግ የትግላችን አንዱ ግብ ነው።

እንደ ሀገር ሰላማዊ የነገዶች መስተጋብር ይኖር ዘንድ የሽግግር ፍትሕ ተግባራዊ መደረግ አለበት። ይህ የሽግግር ፍትሕ ሦስት (3) የአፈጻጸም ደረጃዎች ይኖሩታል።

**ሀ. ዕውነትን ማውጣት (uncover the truth):** የመጀመሪያው ለደረሰው ግፍና በደል በቂ ጥናት አድርጎ ዕውነቱን በማውጣት ብሔራዊ ዕውቅና መስጠት ነው። አስከፊ የተባሉት የዘር ጭፍጨፋዎች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች መደረጉን በብሔራዊ ደረጃ በአዋጅ በማመን ይቅርታ መጠየቅና

existence against any impending threats.

**2nd. Transitional Justice and Lasting Peace**

The Amhara people have endured all forms of barbaric acts. Amhara identity has been treated as a crime. Releasing innocent Amhara people, who are being tormented in known and unknown prisons across the country, as well as all those who have been wrongfully imprisoned and abused without fault, is one of our struggle's goals.

Through the actions of the murderous Prosperity Party and its accomplices, the fate of 17 female Amhara students who have been kidnuped from Dembi Dollo University, along with other Amharas who vanished at various times, will be investigated. Those alive will be reunited with their families; if deceased, their families will receive appropriate support and fair compensation, and the perpetrators will be brought to justice. Furthermore, for the repeated illegal military campaigns against the Amhara people, the lives lost, property destroyed, the economic damage, the disruption of education and health services, and the missed opportunities, the victims and their families will receive adequate compensation. This is one of our struggle's goals.

To ensure peaceful coexistence among the people of the country, transitional justice must be implemented. This transitional justice will have three (3) stages of implementation:

ለመጪው ትውልድ አስተማሪ ሆኖ እንዲያልፍ ብሔራዊ የሰማዕታት ቀን ማወጅ ያስፈልጋል።

**ለ. ወንጀለኞችን ወደ ሕግ ማቅረብ (Justice):** ሁለተኛው ምዕራፍ ጥቃቱን ያደረሱ፣ ያቀነባበሩና የመሩ ግለሰቦች እንዲሁም ቡድኖች በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ ነው።

**ሐ. ብሔራዊ እርቅ እና ካሣ (National Reconcilation and Reparation):** በሦስተኛ ደረጃ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ሥነ-ልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ካሣ መስጠት እና ብሔራዊ እርቅ ማካሄድ ሲሆን፣ ይህም ማለት ተፈናቃዮችን ወደ ነባር መኖሪያ ቦታቸው በመመለስ ማቋቋምን ጭምር ያካትታል። በተጨማሪም በዘላቂነት የሕዝባችን ሰላምና ፍትሕ እንዲረጋገጥ ለሁሉም እኩል የሚቆም የፀጥታ መዋቅር በመዘርጋት የጥይት ድምፅ የማይሰማበትን ሰላማዊ ሀገር መገንባትን ያካትታል።

**3ኛ. አግላይና ሀገር አፍራሽ የሆነውን ሕገ-መንግሥት መቀየር:**

ሕገ - መንግሥት አንዲት ሀገር ከምትተዳደርባቸው ሕጎች ሁሉ የበላይ ሕግ ነው። ይህ ማለት ሕገ-መንግሥቱን የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ እና መመሪያ ተግባራዊ መሆን አይችልም ማለት ነው። ይሁን እንጅ የአማራ ሕዝብ ተነግሮ የማያልቅ ሥርዓታዊ በደልና መድሎ የደረሰበት በአፋኙ የኢሕአዴግ ሠራሽ ሕገ-መንግሥት ነው። የበርካታ ሀገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው ሕገ-መንግሥት የማውጣት ሂደት አራት ዋና ዋና ደረጃዎችን ማለትም፡

**a. Uncover the Truth:** The first stage involves conducting a thorough study of the injustices and abuses suffered and acknowledging the truth at a national level. It is necessary to formally recognize the severe ethnic massacres that occurred in all parts of the country by decree, apologize, and declare a national day of remembrance for martyrs to serve as a lesson for future generations.

**b. Justice for Perpetrators:** The second stage involves bringing individuals and groups who orchestrated, led, and carried out attacks to legal accountability.

**c. National Reconciliation and Reparation:** The third stage involves providing psychological and economic compensation to victims and conducting national reconciliation, which includes returning and rehabilitating displaced people to their original homes.

Additionally, to ensure lasting peace and justice for our people, it includes establishing an equitable security structure for all and building a peaceful country where the sound of gunfire is no longer heard.

**3rd. Changing the Exclusive and Destructive Constitution:**

The constitution is the supreme law that governs a country. This means that no law, regulation, or directive that contradicts the constitution can be implemented. However, the Amhara people have suffered untold systemic injustice and discrimination under the

- የማርቀቅ (Drafting)፣ የውይይት (Deliberation)፣ የአቀባበል/ማላመድ (Adoption) እና ማፅደቅ (Ratification) የሚያካትት ነው። ይሁን እንጅ ኢሕአዴግ መራሹ መንግሥት ሕገ - መንግሥቱን ሲያወጣ እነዚህን ሂደቶች ካለመከተሉም በላይ የአማራ ሕዝብ በየትኛውም ደረጃ በዕውነተኛ ወኪሎች አማካኝነት አልተሳተፈም። በወቅቱ አማራን ለመወከል የተደራጀውን መላ አማራ አንድነት ድርጅት (መአሕድ)ን በማጥፋት በምትኩ ፀረ-አማራና የትሕነግ ጉዳይ አስፈፃሚ የሆነውን የቀድሞ ኢሕዴን የኋላው ብአዴን የአማራ ሕዝብ ተወካይ እንዲሆን ተደርጓል። በመጨረሻም የአማራን ሕዝብ የካደ፣ ኢትዮጵያንም አደጋ ውስጥ የከተተ ሕገ-መንግሥት ሥራ ላይ ውሎ ሚሊዮኖችን ለሞትና ለስደት እንዲጋለጡ አድርጓል። ለአብነትም የሚከተሉትን የሕገ-መንግሥቱን ችግሮች ማየት ይቻላል።

**ሀ.** ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው የሕገ-መንግሥት አወጣጥ ሂደቶችና ደረጃዎችን ያላሟላ በተለይም የአማራን ሕዝብ የገፋና ያገለለ፣ በረቂቅ ዝግጅቱ ላይ ያልተወከለበትና ያልተሳተፈበት እንዲሁም በማፅደቅ ሂደቱም ላይ ያልነበረና ያላፀደቀው ስለሆነ፣

**ለ.** በሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 8 (ከቁ.1-3) የሕዝብ ሉዓላዊነት፣ ስልጣንና ተሳትፎ "ለብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች" ብቻ የሰጠና የ"ክልል" ስያሜ ካገኘው ነገድ [ብሔር] ውጭ ያሉትን ነገዶችና [ብሔረሰቦችና] ዜጎች ሀገር አልባ ያደረገ ስለሆነ፣

**ሐ.** በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 39(1) መገንጠል ገደብ የሌለው መብት ሆኖ መቀመጡ ከአንድነት ይልቅ መገንጠልን የሚያበረታታ መሆኑ፣

oppressive TPLF-made constitution. As demonstrated by the experiences of many countries, the process of drafting a constitution involves four main stages: drafting, deliberation, adoption, and ratification. Yet, the TPLF-led government, when enacting the constitution, not only failed to follow these processes but also prevented the Amhara people from genuinely participating through their representatives at any level. At that time, the All Amhara People's Organization (AAPO), which was organized to represent the Amhara, was destroyed, and in its place, the anti-Amhara and TPLF puppet, the former ANDM (later ADP), was made the representative of the Amhara people. Ultimately, a constitution that betrayed the Amhara people and endangered Ethiopia was put into effect, leading to millions of deaths and displacements. Here are some of the constitutional problems:

a. The constitution-making process failed to meet internationally accepted standards and processes, specifically marginalizing and excluding the Amhara people, who were not represented or involved in its drafting and ratification.

b. Article 8, sub-articles (1-3) on popular sovereignty, power, and participation state "only for nations, nationalities, and peoples," making ethnic groups and citizens living outside the region named after an ethnic group stateless.

c. Article 39(1) of the constitution grants an unlimited right to

**መ.** በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 46(2) “ክልሎች” የተዋቀሩበት መሥፈርቶች (የሕዝብ አሠፋፈር፣ ቋንቋ፣ ማንነትና ፈቃድ) ከዓለማቀፍ አሠራር ያፈነገጠና አማራን ለመጉዳት የተሰላ መሆኑ፣

**ሠ.** በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 49(5) ኦሮሚያ ከአዲስ አበባ ልዩ ጥቅም ሊያገኝ ይገባል በማለት ግጭት ቀስቃሽና ለወረራ የሚያነሳሳ መሆኑ፣

**ረ.** መሠረታዊ የሆኑ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ከሆኑት ውጭ ያሉት በርካታ አንቀጾች የአማራን ሕዝብ ለኅልውና አደጋ ያጋለጡ ስለሆኑ፣ ከሕገ-መንግሥቱ በተጨማሪ በዚሁ መሠረት የወጡ የ”ክልል” ሕገ-መንግሥቶች፣ አዋጆችና ደንቦችም አብዛኞቹ አማራን ያገለሉ ከመሆናቸውም በላይ እነዚህን በመጠቀም የአገዛዙ መዋቅር እስከታች ድረስ ተግባብቶ አጠቃላይ የአማራን ሕዝብ በማጥፋት ላይ ይገኛል። ስለሆነም አፋሕድ የአማራ ሕዝብ ያለ ልዩነት የሚያነሳቸውን የማንነት፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ ጥያቄዎች እንዲመለሱ ለማድረግ የሚያስችል ሀገራዊ አካታችና አሳታፊ በሆነና ዓለም አቀፋዊ የሕገ-መንግሥት ቀረጻ ሂደትን በተከተለ መንገድ አዲስ ሕገ-መንግሥት እንዲቀረጽ ይሠራል። አዲሱ ሕገ-መንግሥት እስኪጸድቅ ድረስ የሽግግር ቻርተር ተቋቁሞ ይቆያል። ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች ሀቀኛ ወኪሎቻቸውን በተአማኒ ሂደት መርጠው ሙሉ ተሳትፎ የሚደረግበትና ዓለማቀፍ አሠራርን በተከተለ መልኩ አዲስ ሕገ-መንግሥት እንዲሁም ከሕገ-መንግሥቱ የሚቀዱ ሕጎችና አሠራሮች ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

## 4ኛ. ትክክለኛ የሆነ የሕዝብ ቆጠራ ማካሄድና የበጀት ቀመር ማሻሻያ ማድረግ፡

የአማራ ሕዝብ ቁጥር ፀረ-አማራ በሆነው በራሡ በመንግሥት ሪፖርት ሳይቀር በአስደንጋጭ ሁኔታ እያሽቆለቆለ መሆኑ ተገልጿል። ቀደም ሲልም በ1999

secession, which promotes secession rather than unity.

d. Article 46(2) of the constitution, which outlines the criteria for regional restructuring (population distribution, language, identity, and will), deviates from international practice and is designed to harm the Amhara.

e. Article 49(5) of the constitution states that Oromia will have special benefits in Addis Ababa, which is provocative and inciting to invasion.

f. Many articles that deviate from fundamental international human and democratic rights have put the Amhara people at risk of extinction.

In addition to the constitution, most regional constitutions, proclamations, and regulations enacted under this framework have marginalized the Amhara and have been used by the regime’s structure to collectively destroy the entire Amhara people. Therefore, AFPO will work to draft a new constitution through a process that addresses the Amhara people’s identity, political, economic, and social demands without discrimination, using a national, inclusive approach that follows international constitutional drafting procedures. Until the new constitution is ratified, a transitional charter will be established. Representatives from all segments of society will be genuinely elected, ensuring full participation, and the new constitution, along with laws and procedures derived from it, will be implemented according to international standards.

## 4th. Conducting an Accurate Census and Revising the Budget Formula:

The Amhara population has been reported by the government itself as

ዓ.ም በነበረ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ በፓርላማ ምክር ቤት በቀረበ ሪፖርት 2.5 ሚሊዮን አማራ ጠፋ ተብሎ ምንም ምርመራ ሳይደረግበት የአንድ ሰሞን አጀንዳ ሆኖ መቅረቱ የአማራ ሕዝብ ምን ያክል የኅልውና አደጋ እንደተጋረጠበትና የያዝነው ትግል ምን ያክል ፍትኃዊ መሆኑንም ጭምር ያረጋግጣል።

ይህ በድንገት በወጣ ሪፖርት ይገለጽ እንጅ ከዚህ ቆጠራ በኋላም ያለምንም ማቋረጥ የአማራን የጅምላ ሞትና ቀብር መስማት የዕለት ከዕለት ዜና ሆኖ ቀጥሏል። የአማራ ሕዝብ በአገዛዙ ሪፖርት በየጊዜው ያሽቆለቆለበት ሁኔታ ከዚህ በታች ባሉት ዋና ዋና ምክንያቶች እንደሆነ ይታመናል:-

1. ፀረ-አማራ በሆነው በአገዛዙ ሤራ ቁጥሩ ሆን ተብሎ በቆጠራ ወይንም በሪፖርት እንዲቀነስ በመደረጉ፣
2. ከክልሉ ውጭ ያለው አማራ በማንነቱ የተነሳ በሚደርስበት ሰቆቃ ምክንያት በስጋት ማንነቱን እንዲደብቅ ወይንም ተገዶ ማንነቱን እንዲቀይር መደረጉ (በማንነታቸው ምክንያት ከወለጋ ሞትን አምልጠው በአማራ ብሔራዊ “ክልል” በተለያዩ የመጠለያ ካምፕ ውስጥ የሚገኙ አማራዊያን እንደገለፁት እና የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ዘገባ ማሳያ ናቸው)፤
3. አማራው በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በጅምላ በመገደሉና በመሰደዱ (በአሁኑ ሰዓት ከኦሮሚያ “ክልል” ተፈናቅለው በድንኳን ያለፍትህ ለዓመታት የተቀመጡት ብቻ ከአንድ ሚሊዮን በላይ መሆናቸው ለዚህ ማሳያ ነው)።

alarmingly declining, a consequence of anti-Amhara policies. Earlier, in 2007, a report presented to the parliament on the population and housing census stated that 2.5 million Amhara had disappeared, yet no investigation was conducted, and the issue was quickly forgotten. This confirms the severe existential threat faced by the Amhara people and the legitimacy of our struggle.

This decline, though revealed in a sudden report, has been continuously exacerbated by the mass killings and burials of Amhara, which remain daily news. The consistent decline in the Amhara population, as reported by the regime, is believed to be due to the following main reasons:

a. The anti-Amhara conspiracy by the regime intentionally reduces the population count in censuses and reports.
b. Amhara living outside their region are forced to hide or change their identity due to the suffering they endure because of their identity (as expressed by Amhara in various refugee camps in the Amhara National Regional State after fleeing death from Wollega, and as indicated by human rights organizations’ reports).
c. The mass killing and displacement of Amhara people in all parts of the country (currently, over one million people displaced from the Oromia region alone have been living in tents without justice for years).

These reasons, among others that require further detailed study, may explain the decline.

ከላይ ባሉት በሦስቱም ምክንያቶች ወይንም በሌሎች ወደፊት ዝርዝር ጥናት በሚጠይቁ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል።

ስለሆነም በመላ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ አማራዎች ትክክለኛ ቁጥራቸው፣ እንዲሁም ተዓማኒ የሕዝብ ስርጭት እና ስብጥር ይፋ እንዲደረግ፤ የአማራ ሕዝብ ቁጥር ሆን ተብሎ የተቀነሰበትም ምክንያት እንዲጣራ ይደረጋል። በተጨማሪም በመንግሥታዊ ሤራ የዚህ ሕዝብ ቁጥር በመቀነሱ ምክንያት በየዓመቱ ሊያገኘው የሚገባውን ነገር ግን የተነፈገውን በጀትና በዚህ ምክንያት ያጣውን ልማትና ዕድገት ማካካሻ እንዲያገኝ ይደረጋል።

## 5ኛ. የሃሰት ትርክትን ማረምና ገዥ ብሔራዊ ትርክት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ

አማራ ክፉኛ የተጎዳበት ተገንጣይ ኃይሎች በፈጠሩት የተዛባ ትርክት ነው። ድርጅታችን ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ላይ ሀገራዊ (ብሔራዊ) ገዥ ትርክት አለ ብሎ አያምንም። ይልቁንም ጎሣዊ፣ ተነፃፃሪና ተፃራሪ የሃሰት ትርክቶች ይበልጥ በስፋት የሚስተዋሉበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን። ይህ ደግሞ እርስበርስ ከመከፋፈሉም በላይ የማያባራ ግጭትን ይፈጥራል፤ ሀገርንም ያፈርሳል።

በመሆኑም ትርክትን በተመለከተ በሁሉም ዘንድ ቅቡልነት ያለው ጠንካራ የሆነ ተነፃፃሪ ትርክት ማቅረብና ሌሎች አግላይና ጎጅ ትርክቶችን በማስተካከል ገዥ ሀገራዊ ትርክት እንዲፈጠር አፋሕድ የበኩሉን ሚና ይወጣል።

## 6ኛ. የወሰን እና ማንነት ጥያቄዎችን በዘላቂነት መመለስ

ታሪክ በግልፅ እንደሚያስቀምጠው አማራው የበዛ ዋጋ እየከፈለ አስከብሯቸው የኖሩት አፅመ-ዕርሥት የነበሩት ቦታዎችን እንደሌሎች በጎሳ ማንነት ታጥሮ በመገንጠል ሀገር ለመመሥረት ከማሰብ ይልቅ ለዘመናት በፍቅርና በመከባበር አብረው ከኖሩ ወንድም ኢትዮጵያውያን ጋር ለመቀጠል በማሰብ

Therefore, AFPO will ensure that the correct number of Amhara people throughout Ethiopia, as well as reliable population distribution and composition, are disclosed. An investigation will be conducted into the reasons for the intentional reduction of the Amhara population. Additionally, efforts will be made to compensate for the budget and development losses the Amhara people incurred annually due to the reduction of their population by government conspiracy.

## 5th. Correcting False Narratives and Adopting a Dominant National Narrative:

The Amhara people have been severely harmed by distorted narratives created by secessionist forces. Our organization does not believe that there is a national (state) dominant narrative in Ethiopia today. Instead, we are witnessing an increasing Prevalence of divisive, relative, and contradictory false narratives. This creates not only division but also incessant conflict, leading to the disintegration of the country.

Therefore, regarding narratives, AFPO will play its part in correcting exclusive and harmful narratives to create a strong, accepted, and unifying national narrative.

## 6th. Permanently Resolving Border and Identity Questions

History clearly shows that the Amhara people have made immense sacrifices to protect their ancestral lands. Instead of seeking to establish states by isolating ethnic identities, they chose to live together with other

በኢትዮጵያዊነት ስም ለዓመታት ብርቱ ዋጋ እየከፈለ የቆየ ሕዝብ መሆኑ ይታወቃል። በተለይም ያለምንም ሕጋዊ መሠረትና ያለ አማራው ተሳትፎ አፋኙ ኢሕአዴግ በራሡ ፍላጎት በርካታ የአማራ ማኅበረሰቦችን ወደሌሎች “ክልሎች” በጉልበት በማካለሉ ከክልሉ ውጭ የሚኖረው አማራ ድምፁ እንዲታፈን፣ ውክልና እንዳያገኝ ይባስ ብሎም በማንነቱ ምክንያት እንዲገደል፣ እንዲሳደድና እንዲፈናቀል ተደርጓል።

ይህን ችግር ለመፍታት በነገዶችች መልካም ፈቃድ (consent of the people) ላይ የተመሠረተ እና ማንነትን፣ ታሪክን እና መልክዓ-ምድርን መሠረት ያደረገ ፌደራላዊ ሥርዓት መገንባት ያስፈልጋል። በጉልበትና በተሳሳተ አሠራር (ከመልክዓ-ምድር፣ ከባህልና ከታሪክ ባልተዛመደ ሁኔታ) በመገንጠል በጥቂት ፖለቲከኞች ፍላጎት ብቻ ያለፍላጎታቸውና ባልተገባ መንገድ ተከልለው የነበሩና ከፍተኛ የሆነ በደል ሲደርስባቸው የኖሩት አማራዎች በጥናት ላይ በመመሥረትና በነገዶች ነፃ ፈቃድ የመልክዓ-ምድር፣ የባህልና ታሪክ አምሳያ ወደሆኑበት አሥተዳደር እንዲካለሉ ይደረጋል። ሆኖም አሠፋፈራቸው ስብጥር የሆነና በማንነታቸው ምክንያት በደል ሲደርስባቸው ለኖሩት የማኅበረሰብ ክፍሎች ለደረሰባቸው በደል የሽግግር ፍትሕ እንዲኖርና በዘላቂነትም ችግሩ እንዲቀረፍ ከራሳቸው ምርጫ እና ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር በሚደረግ ጥልቅ ውይይት የመፍትሄ አቅጣጫ ይቀመጣል። ከዚህም በተጨማሪ ዘላቂ ፍትሕና ሰላምን ለማረጋገጥ ወደፊት በሚኖረው ዕውነተኛ ፌደራላዊ አወቃቀር መሠረት እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ በአካባቢው ባለው አሥተዳደር በማንነታቸው ምክንያት ምንም ዓይነት አድልዖ ሳይደርስባቸው እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል አሠራር ይዘረጋል።

Ethiopian brothers and sisters in love and respect for centuries, sacrificing greatly for Ethiopian identity. This is particularly true for many Amhara communities who were forcibly integrated into other regions without any legal basis or their consent by the oppressive TPLF, leading to the suppression of their voices, denial of representation, and even their killing, displacement, and forced migration due to their identity.

To resolve this issue, it is necessary to build a federal system based on the good will of the people (consent of the people), identity, history, and geography. Amhara communities who were incorporated against their will and suffered severe injustices due to force and flawed practices (not aligned with geography, culture, and history) will be reorganized into administrative structures that reflect their geography, culture, and history, based on studies and the free will of the people. However, for communities with mixed populations who have suffered injustice due to their identity, a solution will be provided through deep discussions based on their choice and with the local community, ensuring transitional justice for the injustices they have suffered and resolving the problem permanently. Additionally, to ensure lasting justice and peace, a system will be established under a true future federal structure, enabling every Ethiopian citizen to participate equally in the local administration without discrimination based on identity.

## 7ኛ. የእኩል ተጠቃሚነት እና በፀጋው ልክ መልማት

አማራ በደረሰበት ፖለቲካዊ ሽፍጥ የምድራችን ድሃ ሕዝብ እንዲሆን ተደርጓል። ይህ ገናና ሕዝብ ለዚህ ውርደት የበቃው ደግሞ ላለፉት ሃምሣ ዓመታት በደረሰበት ስልታዊና መዋቅራዊ በደል መሆኑ አያጠያይቅም። ሕዝባችን አሁንም በባዶ እግሩ የሚሄድ፣ በግብርና ሥራ ባህላዊና ኋላ ቀር የበሬ እርሻ እንዲከተል የተደረገ፣ የንፁህ መጠጥ ውሀ ቅንጦት የሆነበት፣ የተማሩ ልጆቹ ሥራ የማያገኙበት ሕዝብ ሆኗል። አማራው መልማት የሚችሉ እጅግ እምቅ የተፈጥሮ ሃብት ባለቤት (ከአማራው አልፎ ለሌሎችም መትረፍ የሚችሉ ሰፊና ለም መሬት፣ ዓመቱን በሙሉ የሚፈሱ ወንዞች፣ ሃይቆች፣ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ የቱሪስት ማዕከላት እንዲሁም ሰፊ የሰው ሃብት) ያለው ቢሆንም ሥርዓቱ በፈጠረው አድሏዊ አሠራርና የኢኮኖሚ ሸፍጥ ምክንያት እስካሁን ድረስ ሊለሙ አልቻሉም። ስለሆነም በቀጣይ ይህ ኢፍትሓዊ አሠራር ተስተካክሎ ከዚህ በፊት የደረሰበትን ኪሳራ ሊያካክስ የሚችል የመሠረተ-ልማትና በመልማት ፀጋው ልክ እንዲለማ በጥናት ላይ የተመሠረተ የኢኮኖሚ ማሻሻያ እንዲያገኝ ይደረጋል። ዘላቂ ፍትሕን ለማረጋገጥ ግን ሁሉም በእኩል ዓይን የሚታይበትን መልክዓ-ምድራዊ ፌደራሊዝም አወቃቀርን ጥቅም ላይ ማዋል ይሆናል። ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ "ክልሎች" ግፍ የተፈጸመባቸው አማራዎች በያሉበት ሆነው ለደረሰባቸው በደል በሽግግር ፍትህ ፓኬጅ ተገቢ ፍትሕ እንዲያገኙ ሆኖ በዘላቂነት ግን በአካባቢው ባለው አሥተዳደር በሁሉም ዘርፍ ተወዳዳሪ ሆነው መኖር የሚችሉበት አወቃቀር የሚዘረጋ ይሆናል።

## 7th. Equitable Benefit and Development Proportional to Contributions

The Amhara people have been reduced to the poorest people in our land due to political deception. This great people's current predicament is undoubtedly a result of systemic and structural oppression suffered over the past fifty years. Our people s"Ill live in poverty; they are forced to follow traditional and backward ox-plow farming methods; access to clean drinking water is a luxury; and educated youth cannot find jobs. Even though the Amhara region possesses immense natural resources (vast and fertile land that can benefit others beyond Amhara, perennial rivers, lakes, natural and artificial tourist attractions, and a large human resource), these have not been developed due to the regime's discriminatory practices and economic sabotage. Therefore, in the future, this injustice will be corrected, and a study-based economic reform will be implemented to compensate for past losses in infrastructure and develop the region proportionally to Its resources. To ensure lasting justice, this will involve implementing a geographical federalism structure that views everyone equally. Furthermore, Amhara people living in various regions who have suffered specific injustices due to ethnicity and regional affiliation will receive appropriate compensation through a transitional justice package and will be able to live as competitive and self-reliant individuals in their local administration.

## 8ኛ. ሥርዓታዊ ለውጥና ፍትሓዊ የፖለቲካ ውክልና እንዲኖር ማድረግ፣

ትናንት የነበረው አፋኙ የኢሕአዴግም ሆነ አሁን ያለው ጨፍጫፊው የኦሕዴድ መራሹ ብልጽግና ሥርዓት የቆመው በነገዶች መካከል የእርስ በእርስ ግጭት በመፍጠር፣ ሚሊዮኖችን በማፈናቀልና ደም በማፍሰስ ላይ ነው። በተለይም የአማራን ሕዝብ ማኅበራዊ እረፍት በመንሳትና ሞጋች የተባሉ የአማራ ልሂቃንና ዕንቁ ወጣቶች በግፍ እሥር ቤት እየማቀቁ ይገኛሉ፤ ከፊሎቹም አድራሻቸው እንዲጠፋ ተደርጓል። ይህ ሥርዓት አማራን ካላጠፋ እንደማይመለስ የድርጅቱ ቁንጮ አመራሮች ያለሃፍረት ከተናገሯቸውና በተግባር ከፈፀሟቸው ክህደቶች ማረጋገጥ ተችሏል። አሁን ያለውን ሥርዓት አፈጣጠርና ሥነ-ባህሪ ለሚረዳ ሁሉ ከላይ ያስቀመጥናቸውን ግቦች ለማሳካት ይህ ሥርዓት በሕይዎት እያለ ተፈጥሯዊ ባህሪው እንደማይፈቅድ ሁሉም ሰው የሚረዳው ሆኖ እናገኘዋለን። ስለሆነም የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት ዘላቂ ሰላምና ፍትሕን ለማስፈን አሁን ያለውን ዘረኛና ጨፍጫፊ ሥርዓት በመቀየር ፍትሓዊ የስልጣን ባለቤትና የፖለቲካ ውክልና በማረጋገጥ በወንድማማችነትና በዕውነት ላይ የተመሠረተ እና ሕዝባዊ ቅቡልነት ያለው ሀገረ-መንግሥት መመሥረት ቁልፍ የትግላችን ግብ ሆኖ የሚቀጥል ይሆናል።

## 8th. Systemic Change and Equitable Political Representation

The former oppressive TPLF and the current murderous ODP-led Prosperity regime built their systems on creating conflict among ethnic groups, displacing millions, and shedding blood. In particular, they have deprived the Amhara people of social peace, and their insightful scholars and prominent youth are languishing in unjust imprisonment, with some even disappearing. It has been confirmed that the regime’s top leaders openly declared and acted upon their intention not to relent until the Amhara people are destroyed. Anyone who understands the formation and nature of the current regime knows that it is inherently incapable of achieving the goals we have set above. Therefore, the Amhara Fano People’s Organization believes that, to achieve lasting peace and justice, replacing the current ethnic and murderous regime with a system that ensures equitable power and political representation, based on brotherhood and truth, and establishing a nationally accepted state, will be the key goal of our struggle.

## ምዕራፍ ሁለት

## የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት ቁልፍ መርሆዎች

### 2.1 የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት

የኢትዮጵያ የግዛት አንድነት፣ ሉዓላዊነትና፣ ብሔራዊ ጥቅም ሳይሸራረፍ መጠበቅ እንዳለበት ድርጅታችን በፅኑዕ ያምናል። የሃገር ማንነትና መገለጫ የሆኑ የሕዝብ እሴቶች በአግባቡ መጠበቅ እንዳለባቸውም በጽኑዕ ያምናል ለዚህም ተግቶ ይሠራል። ዜጎች ከማንኛውም የውስጥና የውጭ ወራሪ አደጋ ውስጥ እንዳይወድቁ አስተማማኝ የሆነ የፀጥታ መዋቅር እንዲዘረጋ ያደርጋል።

### 2.2 እኩልነትና ነፃነት

የአማራ ሕዝብ ለነፃነት ቀናዒ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ነገዶች ጋር ተከባብሮ መኖር የሚወድ የዕኩልነት ተምሳሌት ሕዝብ ነው። ከዚህ እሴት በመነሳት ለሁሉም እኩል የሆነች ሁሉም ጎሣዎች ተከባብረውና ተሳስበው የሚኖሩባት ሃገር መኖር ለዘላቂ ሰላምና ፍትህ ቁልፍ ጉዳይ ነው። በሀገራችን ያሉ ጎሣዎች፣ ሃይማኖቶች፣ ቋንቋዎች እና ባህሎች የሁላችንም እንደመሆናቸው መጠን ተገቢው ዕውቅናና እንክብካቤ ሊደረግላቸው እንደሚገባ አፋሕድ በፅኑዕ ያምናል።

### 2.3 የሃይማኖትና የመንግሥት መለያየት

መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም። ሃይማኖታዊ መንግሥትም አይኖርም። መንግሥት በሃይማኖት አሠራር ጣልቃ አይገባም፤ ሃይማኖትም በመንግሥት አሠራር ጣልቃ አይገባም።

### 2.4 በትብብር መሥራት

የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት አንድ ወጥ አማራዊ ተቋም እንዲፈጠር አጥብቆ ይሠራል። በተጨማሪም ከማንኛውም ጭቆናንና ዘር ጭፍጨፋን ከሚቃወም

# Chapter Two

## Key Principles of the Amhara Fano People’s Organization

### 2.1 Territorial Integrity and Sovereignty

Our organization strongly believes that Ethiopia's territorial integrity, sovereignty, and national interests must be protected without compromise. It also firmly believes that the national identity and values of the people must be preserved. To achieve this, it will work diligently. It will establish a robust security structure to protect citizens from any internal or external aggression.

### 2.2 Equality and Freedom

The Amhara people are not only lovers of freedom but also a symbol of equality, who cherish coexistence with other peoples. Based on this value, establishing a country where all ethnic groups live together in respect and harmony is crucial for lasting peace and justice. AFPO firmly believes that the ethnic groups, religions, languages, and cultures in our country belong to all of us and therefore deserve proper recognition and care.

### 2.3 Separation of Religion and State

There will be no state religion. There will be no religious government. The government will not interfere in religious affairs, and religion will not interfere in government affairs.

### 2.4 Working in Collaboration

The Amhara Fano People’s Organization will work strenuously to create a unified Amhara institution. Additionally, it has a strong desire to collaborate with any organization

የትኛውም አይነት ፍትሕ ፈላጊ ድርጅት ጋር ተባብሮ የመሥራት ፅኑዕ ፍላጎት አለው። ድርጅታችን ከሁሉም ጭቁን ሕዝብ ጎን ቆሞ የሚታገል ድርጅት ሲሆን ወደፊት ሀገራዊ መንግሥት ለመመሥረትና የዜጎችን ዕኩልነት ለማስፈን በትብብር የሚሠራ ይሆናል።

## 2.5 የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን ማክበር

የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት ለሰብዓዊ መብትቶች መከበር ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይንቀሳቀሳል።

የሰው ልጆች የሰባዓዊነት መርሆች እንዲከበሩ የሚያስችሏቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ያደረገ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ መሠረታዊ የሆነው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ (Universal Declaration of Human Rights) /UDHR/ ነው። በዚህ ዓለም አቀፍ ድንጋጌ መሠረት ማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር ሰው በመሆኑ ብቻ ያገኛቸውን በሕይዎት የመኖር፣ የአካል ደኅንነት፣ የነፃነት መብት እና ከማንኛውም ኢ- ሰብዓዊ አያያዝ የሚጠበቅ መሆኑን ይደነግጋል። የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት ይህን ድንጋጌና ሌሎች አለማቀፍና አህጉራዊ ይዘት ያላቸውን የሰብዓዊ መብት ሕግጋቶችን የማክበርና የማስከበር ግዴታውን ለመወጣት በተቋማዊ ደረጃ ይዞት የሚቀጥል መርህ ይሆናል።

that opposes oppression and ethnic cleansing and seeks justice. Our organization fights alongside all oppressed peoples and will work in cooperation to establish a national government and ensure citizens' equality.

## 2.5 Respect for Human Rights Conventions

The Amhara Fano People's Organization gives special attention to human rights and operates accordingly.

It has adopted international agreements that ensure the observance of human rights principles, including the fundamental Universal Declaration of Human Rights (UDHR). This international declaration states that every human being, simply by being human, has the right to life, physical integrity, freedom, and protection from any inhumane treatment. The Amhara Fano People's Organization will continue to uphold its institutional commitment to respect and enforce this declaration and other international and regional human rights laws.

AMHARA FANO PEOPLE'S ORGANIZATION

## ምዕራፍ ሦስት

## የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት ፕሮግራሞች

### 3.1 የፖለቲካ ፕሮግራም

የአማራ ሕዝብ በተከታታይ የአገዛዙን ወንበር በተቆናጠጡ ፀረ-አማራ ኃይሎች ፖለቲካዊ ሽፍጥና ክህደት ተፈጽሞበታል። በባህሉ፣ በእሴቱ፣ በክብሩና በታሪኩ ሁሉ ጥቃትና ማጥላላት ተፈጽሞበታል፤ በማንነቱ ምክንያት የዘር ፍጅት ተካሂዶበታል።

በመሆኑም የአማራ ሕዝብ የደረሰበትን ጥቃትና ዘር ፍጅት አክሞ ወደ ሽግግር ፍትሕ የሚወስድ ከሌሎች በተመሳሳይ ሂደት ካለፉ ሀገሮች ልምድ በመቅሰም የኢትዮጵያ ዕውነት አፈላላጊና እርቅ ኮሚሽን ይቋቋማል። በጥናት የተመሠረተ ገዥ ትርክት፣ ፍትሕ እና ብሔራዊ እርቅ እንዲመጣ ይደረጋል።

#### 3.1.1 የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና የሰብዓዊ መብቶች መከበር

በሁሉም አሠራሮች ውስጥ የሕግ የበላይነትን በማስፈን ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ይከበራሉ። ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውና ያፀደቀቻቸው ዓለም-አቀፋዊና አህጉራዊ ሕጎችና ድንጋጌዎች እንደነባራዊ ሁኔታው እየታዩ ተቀባይነት ይኖራቸዋል። ሀገራችን በተለያዩ ወቅቶች የተቀበለቻቸው እና ያወጣቻቸው ሕጎች የዜጎችን መብት ይጥሳሉ፣ ወይም ይገድባሉ ተብለው ከታመነባቸው ሊሻሻሉ ወይም ሊሰረዙ ይችላሉ። ዜጎች ሃሳባቸውን በነፃነት የመግለጽ መብታቸው እንዲከበር ይደረጋል። የተለያዩ የሲቪክ ማኅበር አደረጃጀቶች እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ ይደረጋል። ሕፃናትን፣ ሴቶችንና አካል ጉዳተኞችን

## Chapter Three

## Amhara Fano People's Organization Programs

### 3.1 Political Programs

The Amhara people have been subjected to political deception and betrayal by anti-Amhara forces who have successively seized power. Their culture, values, dignity, and history have been attacked and tarnished, and ethnic cleansing has been carried out against them due to their identity.

Therefore, to heal the damage and ethnic cleansing suffered by the Amhara people and to move towards transitional justice, an Ethiopian Truth-Finding and Reconciliation Commission will be established, drawing lessons from other countries that have undergone similar processes. This will lead to the establishment of a truth-based dominant narrative, justice, and national reconciliation.

#### 3.1.1 Building a Democratic System and Respect for Human Rights

The rule of law will be upheld in all processes, ensuring respect for democratic and human rights. International and regional laws and conventions that Ethiopia has ratified will be accepted and applied in accordance with existing circumstances. Laws that have been adopted by our country at various times and are believed to violate or restrict citizens' rights may be amended or repealed. Citizens' right to freedom of expression will be protected. The establishment and strengthening of various civil society organizations will be promoted. Regarding children, women, and persons with disabilities, special protective laws will be enacted, taking into account national

በተመለከተ ከዓለምአቀፍ ሕጎች በተጨማሪ ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታውን ያገናዘበ ልዩ ጥበቃ የሚሰጥ ሕግ እንዲወጣ ይደረጋል። ሰብዓዊ መብት ተፈጥሮ ለሰው ልጆች የሰጠው የማይገሰስ ፀጋ ነው። አፋሕድ ወደ ትግል ከገባባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል አንዱ የዜጎች ሰብዓዊ መብት መጣስና የኅልውና አደጋ ውስጥ መውደቅ በመሆኑ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል። ይህ መብት እንዳይሸራረፍና በጉልበተኞች እጅ እንዳይወድቅ ከመንግሥታዊ መዋቅር ውጭ በሆነና ነፃና ገለልተኛ ተቋማት ልዩ ጥበቃ እንዲያደርጉለት እንዲሁም የዓለማቀፍ የሰብዓዊ ተቋማት በቅርበት የሚከታተሉት አሠራር ይዘረጋል።

### 3.1.2 የመንግሥት ስልጣን አወቃቀር

ኢትዮጵያ ውስጥ በአንድነትና በብዝኃነት (Unity vs Diversity) መካከል ከፍተኛ ውጥረት እንደነገሠ ይታወቃል። አንዳንዶች ከብዝኃነት ይልቅ በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ብቻ ትኩረት እንዲሰጥ የሚፈልጉ እንዲሁም አወቃቀሩ ለዚሁ በሚጠቅም መልኩ እንዲሆን ይፈልጋሉ። ሌሎች ደግሞ በማንነት ላይ ትኩረት እንዲደረግና እስከ መገንጠል በመሄድ የኢትዮጵያን መቀጠል የሚፈታተን ፍላጎት እያሳዩ ይገኛሉ።

ድርጅታችን ከነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ቀጣዩ የመንግሥት አወቃቀር የኢትዮጵያን መቀጠልና የማንነት ፍላጎቶች የሚታረቁበትን አውድ ለመፍጠር ይሠራል። በማንነቱ ምክንያት ጥቃት እየደረሰበትም እንኳን የአማራ ሕዝብ አማራነቱ (ነገዳዊ ማንነቱ) ከኢትዮጵያዊነቱ (የዜግነት ማንነቱ) ጋር ተጋጭቶበት አያውቅም።

ከዚህም በተጨማሪ የመንግሥት አወቃቀሩን በተመለከተ በቀጣይ ሀገር ምሥረታ ላይ በሚደረጉ ሁሉን አሳታፊ ውይይቶች የሚወሰን ይሆናል። ሆኖም ድርጅታችን ሀገራዊ አንድነትን በሚያጎሉ እና ከመነጣጠል ይልቅ በመተሳሰብ ላይ እንዲሁም ሀገራዊ ማንነት ላይ ትኩረት በመስጠት እኩልነትና ፍትሕ እንዲሁም ዘላቂ ሰላምንና አንድነትን

realities in addition to international laws. Human rights are an inviolable gift of nature to human beings. AFPO gives special attention to the protection of human rights because the violation of citizens' human rights and their existential threat were among the main reasons for its struggle. A system will be established, outside the government structure, with independent and impartial institutions to provide special protection for this right, ensuring it is not eroded or manipulated by powerful individuals, and international human rights organizations closely monitor it.

### 3.1.2 Government Structure

In Ethiopia, it is known that there is significant tension between unity and diversity. Some want to prioritize Ethiopia's unity over diversity and desire a structure that supports this. Others prioritize identity, even advocating for secession, and challenge Ethiopia's continuity.

Our organization will work to create a framework that reconciles Ethiopia's continuity and identity aspirations, based on existing realities. The Amhara people, even though they have suffered attacks due to their identity, have never seen their Amhara identity (ethnic identity) clash with their Ethiopian identity (citizenship identity).

Furthermore, regarding the government structure, the decision will be made through inclusive discussions on future nation-building. However, our organization strongly believes in promoting national unity, interdependence rather than division, and national identity to achieve equality, justice, and lasting peace. To achieve this, it will propose alternative ideas for a progressive federal system that ensures

እናመጣለን የሚል ፅኑዕ ዕምነት አለው። ለዚህም ስኬት ሲባል ሁሉም ዜጋ በሀገሩ የሚኮራበትና በየትኛውም ቦታ ያለስጋት ሠርቶ የሚከብርበትና እኩል ተወዳዳሪ የሚሆንበት ሂደታዊ የፌዴራላዊ ሥርዓት አወቃቀር እንዲኖር አማራጭ ሃሳብ ይዞ ይቀርባል።

በሚከተሉት አማራጭ ሃሳቦችም ትኩረት አድርጎ ይሠራል።

**ሀ/** የአማራ ሕዝብ ብሎም የኢትዮጵያ ሕዝብ ተራማጅና የስልጣኔ ባለቤት እንደመሆኑ መጠን ባህሉን፣ ሃይማኖቱን እና እሴቱን ጠብቆ የዘመናዊው ዓለም ከሚራመድበት ሁለንተናዊ ዕድገት ጋር የሚጣጣም ቅይጥ ርዕዮት-ዓለም (Ideology) ጠቃሚ እንደሆነ ይገነዘባል። ስለሆነም ተራማጅ የሆነ ነገር ግን የሺህ ዘመን እሴትን የሚጠብቅ ፕራግማቲዝም (pragmatism) ርዕዮት-ዓለም ይከተላል።

**ለ/** የአገር አስተዳደር መዋቅሩ ሂደታዊ ፌደራላዊ ሥርዓትን የተከተለ ይሆናል። የፌዴራል አስተዳደር ግዛቶች ሲዋቀሩ ለልማትና ለአስተዳደር አመቺነትን፤ የሕዝብ አሰፋፈርንና ፍላጎትን፤ የታሪክና የሥነ-ልቦና ትስስርን፣ የመልክዓ-ምድር አቀማመጥን መሠረት ማድረግ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁሉን አሳታፊ በሆነ ውይይት የሚወሰን ይሆናል።

**ሐ/** የፌደራል መንግሥቱና የፌደራል መንግሥቱ አባላት (ክፍለ-ሀገሮች) ተለይቶ የሚሰጣቸው ሥልጣንና ሃላፊነት በሕግ ይወሰናል።

**መ/** አማርኛ አገራዊ የሥራ ቋንቋ ሆኖ ይቀጥላል። ሆኖም በጥናት ላይ በመመሥረት ሌሎች ቋንቋዎች በተጨማሪነት ሥራ ላይ ሊውሉ ይችላሉ።

**ሠ/** የፌደራል መንግሥቱ ሦስት የሥልጣን አካላት ይኖሩታል። እነሱም ሕግ አውጭ፤ ሕግ ተርጓሚና ሕግ አስፈጻሚ ናቸው። እነዚህ የሥልጣን አካላት አንዱ ከሌላው ገለልተኛ እና የየራሳቸው የሥራ ድርሻ ኖሯቸው አንዱ ሌላውን እንዲቆጣጠር (check and balance) ተደርገው ይዋቀራሉ። ይህ የፌደራሉ መንግሥት

every citizen is proud of their country, lives and works without fear anywhere, and can compete equally.

**a.** Recognizing the Amhara people and the Ethiopian people as progressive and civilized, our organization understands that their culture, religion, and values, combined with a modern worldview that aligns with global development, are beneficial. Therefore, it follows a pragmatic ideology that is progressive but preserves centuries-old values.

**b.** The country's administrative structure will follow a progressive federal system. When structuring federal administrative territories, considerations will include convenience for development and administration, population distribution and desires, historical and psychological ties, and geographical location, all to be determined through inclusive discussions.

**c.** The powers and responsibilities of the federal government and its member states (regions) will be defined by law.

**d.** Amharic will continue to be the national working language. However, other languages may be adopted for use based on studies.

**e.** The federal government will have three branches of power: legislative, judiciary, and executive. These branches will be independent of each other and will have their own duties, structured to ensure checks and balances. This federal government structure will also be implemented similarly in the member states.

**f.** The political system will be multi-party. The electoral system will follow international standards and be

አወቃቀር በፌደራሉ አባል ግዛቶችም በተመሳሳይ መልኩ ተግባራዊ ይደረጋል።

ረ/ የፖለቲካ ሥርዓቱ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓትን የተከተለ ይሆናል። የምርጫ ሥርዓቱም ዓለማቀፍ ሥርዓቱን የጠበቀ ሆኖ ተመጣጣኝ (proportional) እና በየአምስት ዓመቱ የሚካሄድ ይሆናል። መንግሥታዊ ሥርዓቱም በሂደት ወደ ፕሬዚዳንታዊ ሥርዓት ይሸጋገራል።

### 3.1.3 የውጭ ግንኙነት

የውጭ ግንኙነት መርሃችን የሀገርና ሕዝብ ዘላቂ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ይሆናል። ከዚህ በተቃራኒ የተደረጉ የውጭ ግንኙነት ውሎችና ስምምነቶች ሕጉን መሰረት ባደረገ መልኩ ሊሻሻሉ ወይም ፈፅሞ ሊሰረዙ ይችላሉ። በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ዜጎች ክብራቸው ተጠብቆ እንዲኖሩ ያላሰለሰ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ይደረጋል። ለአፍሪካ ሕዝቦች ዘላቂ አንድነትንና ሁለገብ እድገት ማምጣት ከአንኳር ግቦቻችን መካከል አንዱ ሲሆን፣ ይህንን ግብ ለማሳካት ዋናው ስትራቴጂያችን የአፍሪካ ሀገራትን በጋራ የልማትና የሰላም ጥረቶች በማስተሳሰር የጋራ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ይሆናል።

### 3.1.4 የሽግግር ጊዜ

ከድል ማግስት፣ የኢትዮጵያን ሀገረ መንግሥት ቅርፅና አወቃቀር እንዲሁም ስልጣን ለመወሰን ሁሉን አቀፍና አካታች ውይይት ይደረጋል። በዚህ ውይይት ሁሉም ነገዶች በእኩልነትና ትርጉም ባለው ውክልና እንዲሳተፉ ይደረጋል። ከአምስት አመት የሽግግር ጊዜ በኋላም በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት ይመሠረታል።

የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት አፋኙ የኢሕአዴግና ጨፍጫፊው ብልጽግና የተከተሉት ጎሳ ተኮር ፖለቲካ ዜጎች በማንነታቸው ብቻ የተለየ ተጠቃሚ ወይም ተጎጅ ሲያደርግ መቆየቱ ለከፋ ቀውስ ዳርጓል ብሎ ያምናል። እንደ ሀገር ተፈጥረው የቆዩ ደም አፋሳሽ ልዩነቶችን በወጉ ለማከም ይረዳ ዘንድ ብሔራዊ እርቅንና አካታች የሀገር ምሥረታ ያስፈልጋል። ዜጎች

proportional, held every five years. The governmental system will gradually transition to a presidential system.

### 3.1.3 Foreign Relations

Our foreign policy will be based on the lasting interests of the country and its people. Foreign relations agreements and treaties made in contradiction to this may be revised or completely repealed based on the law. Relentless diplomatic efforts will be made to ensure that citizens living abroad live with dignity.

Bringing about lasting unity for the peoples of Africa is one of our core objectives, which includes building a strong African leadership role that benefits common prosperity and development. The main strategy to achieve this goal is to ensure mutual benefit by connecting the continent's countries through joint development and peace efforts.

### 3.1.4 Transitional Period

After victory, an inclusive and comprehensive discussion will be held to determine the form and structure of Ethiopia's state and power. All ethnic groups will participate equally and meaningfully in this discussion. A government elected by the people will be established after a five-year transitional period.

The Amhara Fano People’s Organization believes that the TPLF's oppressive and the Prosperity Party's murderous ethnic-based politics, which have caused citizens to be privileged or harmed solely based on their identity, have led to a severe crisis. To properly heal the deep-seated divisions that have arisen in the country, national reconciliation and inclusive nation-building

ሰው ሆነው በመፈጠራቸው ብቻ የማይገሰስ ተፈጥሯዊ መብት እንዲሁም የማንነትና ሌሎች የቡድንና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን ሊጎናፀፉ ይገባል።

ስለሆነም ልዩ ልዩ ምሑራንና ባለሙያዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ሴቶች፣ የኃይማኖት አባቶች፣ ሲቪክ ማኅበራት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የነፃነት ታጋዮች፣ ነገዶችና ሌሎችም ጭምር የተካተቱበት ከችግሩ ምንጭ እስከ መፍትሔው ድረስ በሚደረግ ሀገራዊ ውይይትና ምክክር ከተፃራሪ ትርክቶች ይልቅ ገዥ የሆነ ሀገራዊ ትርክት እንዲፈጠርና የጋራ ዕጣ ፈንታም እንዲኖረን የሽግግር ምክረ ሃሳብ ይቀርባል። እነዚህ ውይይቶች በማንነት ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎችና የዘር ፍጅቶች እንዲሁም ስልታዊ ጥቃቶች ዕውቅናና የሽግግር ፍትሕ (Transitional Justice) አግኝተው መሄዳቸው የጥላቻና የመጠራጠር ጊዜ አብቅቶ ፍትሕ፣ ዕኩልነትና ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት መሠረት እንደሚጥሉ ይታመናል። ይህ ሂደት በመተማመን ላይ የተመሠረተ ጠንካራ ሀገራዊ አንድነት እንዲፈጠር ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል።

## 3.2 የኢኮኖሚና የዕድገት ፕሮግራሞች

የአማራ ሕዝብ ላለፉት ሃምሳ ዓመታት ጨፍጫፊና አምባገነን የሆኑ ሥርዓቶችን በማስተናገዱ ምክንያት ከባድ የሆነ ሰብዓዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ውድመት እየደረሰበት ይገኛል።

የአንድን ሀገር ግጭት ለመቀነስም ሆነ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ፍትሓዊ የኢኮኖሚና የሰብዓዊ ልማት ማምጣት ቁልፍ መፍትሔ ነው። እንደ ሀገር ከፍተኛ እድገት ሊያመጡ የሚችሉ ዘርፎችን በተለይም የሰው ኃብት ልማት፣ መሬት፣ ግብርና፣ መሰረተ-ልማት፣ ንግድና ኢንዱስትሪ እንዲሁም ቱሪዝም ላይ የሚደረጉ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል፡፡

### 3.2.1. የሰው ሀብት ልማት

የጠንካራ ኢኮኖሚ ዋናው የጀርባ አጥንት የሰለጠነ የሰው ሀብት ነው። ላለፉት ተከታታይ አስርት

are necessary. Citizens, by virtue of being human, should enjoy their inalienable natural rights, as well as their identity and other group and democratic rights.

Therefore, a transitional proposal will be submitted, incorporating the views of various scholars and experts, community elders, women, religious leaders, civil society organizations, political parties, freedom fighters, ethnic groups, and others, through national discussions and consultations, to create a unifying national narrative instead of conflicting ones, and to ensure a common destiny. These discussions, by acknowledging and addressing crimes against identity and ethnic cleansing, as well as systematic attacks, are believed to lay the foundation for justice, equality, and lasting peace, ending the era of hatred and suspicion. This process will play a significant role in establishing a strong national unity based on trust.

## 3.2 Economic Programs

The Amhara people have been reduced to the poorest people in our land due to systematic economic attacks. For the past fifty years, the Amhara people have endured murderous regimes. Currently, under the ODP-led Prosperity regime, a devastating war is being waged, causing severe human, economic, and social destruction. Existing heritage sites and initiated infrastructure projects are being completely destroyed. Therefore, a special economic compensation and the rebuilding of the destroyed infrastructures program is needed for the damage suffered due to war and systematic attacks.

### 3.2.1. Human Resources Development

The backbone of a strong economy is skilled manpower. For the past decades, the

አመታት ኢትዮጵያን ያስተዳደሩ መንግስታት ትውልዱን በተለይም ወጣቱን የሀገር ጸጋ ከማድረግ ይልቅ ለፖለቲካ ፍላጎት መጠቀሚያ ሲያደርጉ መቆየታቸው ሀገር በከፍተኛ ድህነትና ኋላቀርነት ችግር ውስጥ እንድትገባ አድርጓታል። በቴክኒክና ሙያ ስልጠና እንዲሁም አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ያለው እንቅስቃሴ ተወዳዳሪነትን የሚያበረታታ ሳይሆን ለሥርዓቱ ባለ ቅርበትና ታማኝነት ላይ የተመሰረተና በምርጫ ወቅት ድጋፍ ለማግኘት ታስቦ የተሰራ ስለሆነ ወጣቱን እና ሀገርን አንድ እርምጃ ሊያሻግር አልቻለም።

አሁን ያለው አምባገነን ሥርዓት የሀገሪቱ በጀት ፍትሓዊ ለሆነ እና በድህነት ውስጥ የሚማቅቀውን ሕዝባችንን ህይወት ሊቀይር የሚችል እድገት ተኮር ልማት ከመስራት ይልቅ በመቶ ቢሊዮን በጀት የሀገሪቱ አንጡራ ሃብት "የገበታ ፕሮጀክት" እና "የኮሪደር ልማት" በሚል ለአምባገነኑ ባለስልጣናትና አጋሮቻቸው ስሜት ማርኪያ አብለጭላጭ ስራዎች እየዋለ ይገኛል፡፡ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚኖረው ማሕበረሰብ ፋይዳ የሌላቸው እነዚህ የቅንጦት ፕሮጀክቶች የሕዝብን ችግር በመጋረድ የአገዛዙን ውድቀት ለመሸፈን ከፍተኛ ፕሮፖጋንዳ እየተሰራባቸውም ይገኛል፡፡ የአምባገነኑ ሥርዓት የልማትና ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማኅበረሰቡን በተለይም ወጣትን ማዕከል ያደረገ ባለመሆኑ ግዙፍ የሆነው አምራች ወጣት በሀገሩ ተስፋ ቆርጦ በረሃ እና ባህር አቋርጦ ለመሰደድ ተዳርጓል። አንዳንዶች ለአገዛዙ ሎሌ ሆነው ሕዝባቸውን ሲጨቁኑ አብዛኛው ወጣት ደግሞ የተሻለ አማራጭ በማጣት ከልማት ውጭ ሆኖ በአልባሌ ቦታዎች እንዲባክን ተደርጓል፡፡

ስለሆነም አፋሕድ ግዙፍ የልማት አቅም የሆነውን ወጣት በእውቀትና በአመለካከት በማሳደግ ለስራ ፈጠራና ለልማት ቆርጦ እንዲነሳ የሚያደርግ ፖሊሲና ስትራቴጂ ቀርፆ ወደ ተግባር ይገባል፡፡ ብዙኃኑን የማሕበረሰብ ክፍል ተጠቃሚ የሚያደርጉ

governments that have ruled Ethiopia have exploited the generation—especially the youth—for their political gains rather than turning them into a blessing for the country, which has led to extreme poverty and backwardness. Activities in technical and vocational training, as well as in small and medium enterprises, were not designed to promote competitiveness but were based on nepotism and loyalty to the system, aimed at gaining support during elections, and have failed to advance the youth and the country even a single step.

The current authoritarian regime is spending hundreds of billions of the country's budget on the "Gebeta Project" and "Corridor Development" to satisfy dictatorial authorities and their allies, instead of investing in growth-oriented development programs that could improve the lives of our people living in poverty. These luxury projects, which are of no use to the lower class, are being used as propaganda tools to conceal the regime's collapse by hiding the people's real problems. Since the development and economic activities of the dictatorial regime do not center on the community—especially the youth, who are the main producers in the country—many have been forced to migrate across vast deserts and seas. Others are compelled to serve the regime and oppress their own people, whereas most of the youth have been left in poverty without any better options.

Therefore, AFPO will formulate and implement policies and strategies that empower the youth—who possess immense development potential—with knowledge and perspective, making them determined to create jobs and contribute to national development. Development projects that benefit the majority of society will be implemented in a planned manner. In this way, various strategies will be designed and

የልማት ፕሮጀክቶች በተጠና መንገድ ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ በዚህም ሰፊው የሰው ኃብታችን በአግባቡ እንዲለማ በማደረግ ለሁሉም አይነት የኢኮኖሚ ሴክተሮች ማዕከላዊ ሞተር ሆኖ ሁለገብ እድገት እንዲመዘገብ ልዩ ልዩ ስትራቴጂ ተነድፎ የሚሰራ ይሆናል፡፡

### 3.2.2 የመሬት ባለቤትነት

ለአማራ ሕዝብ መሬት ለብዙ ሺህ ዓመታት በዕርሥትነት ሲያስተላልፈው የቆየ ቋሚ ኃብት ብቻ ሳይሆን ማንነቱም ጭምር ነው። ይሁን እንጅ ከ1960ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ አዲስ አበባን ጨምሮ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል ከመሬቱና ዕርስቱ "ሰፋሪ"፣ "ወራሪ"፣ "ተስፋፊ"፣ "መጤ" "ነፍጠኛ" እና የመሳሰሉ የማጥቂያ የኮድ ስያሜዎች እየተሰጠው እንዲፈናቀል ተደርጓል፤ ያለአግባብ መሬቱና ዕርስቱ ተወስዶበታል። በመሆኑም ይህን የሚያጠና የዕውነትና የእርቅ ኮሚሽን ይቋቋማል። ኮሚሽኑም ከበቂ ጥናት በኋላ አማራን ለማፈናቀል የወጡ ሕጎችን በመሻር አዲስና ሚዛናዊ ሕግ እንዲወጣ ይደረጋል። የመሬት ይዞታ የግለሰብ፤ የመንግሥት፣ የእምነት ተቋማትና የኅብረተሰብ በሚል በአራት አካላት ሥር እንዲሆን ይደረጋል። ይህን በማይጣረስ መልኩ የገጠርም ይሁን የከተማን የግል ይዞታ፣ መሬት መሸጥና መለወጥን፣ ከባንክ ለመበደር ዋስትና ማድረግ፣ እንዲሁም ለሦስተኛ አካል በውርስ ማስተላለፍ የሚቻልበት ሕግ ይሻሻላል።

የመንግሥት የምንላቸው መሬቶች የመንግሥታዊ ተቋማት ቦታዎች፣ ጥብቅ ደኖችና ፓርኮች ይሆናሉ። እነዚህ መሬቶች በመንግሥት ይዞታ ውስጥ ሆነው ለሕዝብ ጠቀሜታ የሚውሉ ይሆናሉ። የአርብቶ አደር የግጦሽ ቦታዎች፣ ባህላዊ ተግባራትን ለማከናወን የሚውሉ ቦታዎች፣ ለማኅበራዊ አገልግሎት የሚውሉ ቦታዎች የወል መሬቶች ሲሆኑ፣ ባለቤትነታቸው የሕብረተሰቡ ይሆናል።

executed to ensure that our vast human resources are properly developed and become the central engine of all economic sectors, thereby achieving all-round growth and development.

### 3.2.2 Land Ownership

For the Amhara people, land has been not only a permanent resource passed down through generations for thousands of years but also their identity. However, since the late 1960s, Amhara people in Addis Ababa and other parts of the country have been evicted from their land and property under derogatory labels such as "settlers," "invaders," "expansionists," "bearer of gun" and "aliens." Therefore, a truth and reconciliation commission will be established to study this issue. After thorough study, the commission will repeal the laws that led to the displacement of Amhara and enact new balanced laws. Land ownership will be structured under four categories: individual, government, religious institutions, and community. Laws will be amended to allow for the sale, exchange, banking, and inheritance of rural and urban private land.

Government lands will include government institutional properties, protected forests, and national parks. These lands will remain under government ownership and be utilized for public benefit. Pastoral grazing lands, areas for cultural activities, and public service lands will be communal, with ownership belonging to the community.

Lands designated for religious institutions and any religious activities will be under the ownership of their respective followers.

የቤተ እምነት ቦታዎች እና ለማንኛውም ሃይማኖታዊ ክንውኖች የሚውሉ መሬቶች በሃይማኖቱ ተከታዮች ሥር ይሆናሉ።

### 3.2.3 ግብርና

ግብርና ለአማራና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዋነኛ የኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት መሆኑን እንገነዘባለን። ስለሆነም ድርጅታችን የግብርና ሥርዓቱን በማዘመንና መዋቅራዊ ሽግግር በመፍጠር ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ትኩረት ይሰጣል። የመሬትን ለምነት ለማሻሻል ወይንም ጠብቆ ለማቆየት አስፈላጊ የሆኑ ፕሮግራሞች ተነድፈው ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል። ወጣቶችን ወደ ሥራ በሚያስገባ እና የሀገርን የምርት መጠን በከፍተኛ ደረጃ ለማሻሻል ሰፋፊ የእርሻ ሜካናይዜሽን ሥራ ይሠራል።

### 3.2.4 ኢንዱስትሪ

የአማራ ሕዝብ በኢንዱስትሪ መሠረተ ልማቶች ጭራ ተብሎ የሚገለፅ ነው። ያለፉት ሥርዓቶች ለአማራ ሕዝብ ሊጠቅም የሚችል ከመጠጥ ፋብሪካ ወይንም ከኢንዱስትሪ ሸድና ጥቃቅን ፋብሪካዎች ያለፈ ነገር አልተሠራለትም። በመሆኑም ይህን ታሪክ ሊቀይር የሚችል ከግብርናው ጋር ተመጋጋቢ የሆኑ፤ ለወጣቶች የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ፤ ከተሜነትን የሚያመጡ የኢንዱስትሪ አማራጮች እየተገመገሙ በጥናት ይገነባሉ። በተጨማሪም ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸው የረቀቀ ቴክኖሎጂና ከፍተኛ ካፒታልን የማይጠይቁ እንዲሁም የኢትዮጵያን ተፈጥሯዊ ጸጋዎች በቀላሉ የሚጠቀሙ ልዩ የኢንዱስትሪ ተቋማት እንዲመሠረቱ ድጋፍ ይደረጋል።

### 3.2.5 ንግድ

የንግድ ሥርዓቱ ነፃና ፍትሓዊነትን የሚያበረታታ ሆኖ ይዘረጋል። የንግድ ሥርዓቱ የሕዝብን እና የሀገርን ጥቅም ያማከለ፣ የግል ክፍለ-ኢኮኖሚ ተኮር የነፃ ገበያ ሥርዓትን የሚያበረታታና የገበያ ተወዳዳሪነትን የሚፈጥር እንዲሆን ይደረጋል። ሆኖም በተመረጡና ሕዝብን የተሻለ ተጠቃሚ በሚያደርጉ የንግድ ዘርፎች

### 3.2.3 Agriculture

We recognize that agriculture is the backbone of the Amhara and Ethiopian economy. Therefore, our organization will focus on modernizing the agricultural system and implementing structural changes to increase production and productivity. Programs will be developed and implemented to improve or maintain land fertility. It will undertake large-scale mechanized farming to engage youth in work and significantly increase the country's production volume.

### 3.2.4 Industry

The Amhara people are considered lagging in industrial infrastructure. Past regimes have only provided the Amhara people with small-scale factories, such as beverage plants, or micro-enterprises. Therefore, this history will be changed by evaluating and building industrial options that are complementary to agriculture, create jobs for youth, and promote urbanization. Additionally, support will be provided for the establishment of specialized industries that have strategic importance, do not require high technology and capital, and utilize Ethiopia's natural resources effectively.

### 3.2.5 Trade

The trade system will be free and fair. The trade system will be organized to prioritize the interests of the people and the country, promote a private sector-led free market, and foster competition. However, in selected trade sectors and services, or when preserving national values is paramount, the government will intervene.

እና አገልግሎቶች ወይንም የሀገርን እሴት መጠበቅ ቅድሚያ የሚሰጠው ሆኖ ሲገኝ መንግሥት ጣልቃ የሚገባ ይሆናል።

### 3.2.6 መሠረተ ልማቶች

ድርጅታችን መሰረተ ልማቶች የዕድገት ማስፈንጠሪያዎች ናቸው ብሎ ያምናል። በመሆኑም የመንገድ፣ የመብራት፣ የንፁህ መጠጥ ውኃ ግንባታዎች፣ የመገናኛ አውታሮችና ሌሎች ማኅበራዊ መሰረተ ልማቶች ከመንግሥት በተጨማሪ በግሉ ባለሐብቶች እንዲቀርቡ ይደረጋል። የአየር፣ የውኃ፣ የየብስና የባቡር መጓጓዣ ዘዴዎች ዘመኑን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ይገነባሉ።

### 3.2.7 የቱሪዝም ሃብት አንድ ላይ

የአማራ ሕዝብ አስደናቂ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ የቱሪዝም መስህቦች ባለቤት ነው። ኢትዮጵያ ለዓለም ሃብትነት ይበቁ ዘንድ ካስመዘገበቻቸው የተለያዩ ቅርሶች ውስጥ እጅግ አስደናቂዎቹ በአማራ ሕዝብ ግዛት የሚገኙት ናቸው። ድርጅታችን ከእነዚህም በተጨማሪ የሚገኙ ሃብቶችን በጥናትና በምርምር ፋይዳቸውን በማጎልበት፤ መሠረተ ልማት ባልደረሰባቸው መሠረተ ልማትን በመዘርጋትና ከአገልግሎት ሰጭዎች እይታ የራቁትን በማቅረብ ከፍ ያለ የቱሪዝም ገቢ ምንጭነትን ለማጎልበትና የሕዝቡን ቀዳሚ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ይሰራል።

## 3.3 ማኅበራዊ ፕሮግራሞች

### 3.3.1 ትምህርት

ትምህርት የዕድገትና የሥልጣኔ መክፈቻ ቁልፍ ነው። ስለሆነም ማንኛውም ዜጋ ትምህርት የማግኘት ዕድልና ነፃነት እንዲኖረው ይደረጋል።

በኢትዮጵያ ያለው የትምህርት ሥርዓት ትምህርትን አጠናቆ ከፍተኛ ውጤት አምጥቶ መጨረሻ ላይ ስራ ፈላጊ እንጂ ስራ ፈጣሪ ሊያደርግ የሚችል አሰራር ባለመዘርጋቱ ብዙ የተማሩ ወጣቶች ካልተማሩት ወጣቶች እኩል ስራ ፈላጊ መሆናቸው በኢትዮጵያ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የተተገበረው የትምህርት ፖሊሲ ትውልዱን አምራች እና ለሀገር ጥቅም እንዳይውል አድርጎታል።

### 3.2.6 Infrastructure

Our organization believes that infrastructure is a catalyst for development. Therefore, road, , electricity, clean water supply, communication and other necessary social infrastructures will be provided by the government, as well as by private investors. Air, water, land, and train transport systems will be developed in a manner that considers modern times.

### 3.2.7 Tourism Resources

The Amhara people possess astonishing natural and man-made tourist attractions. Ethiopia's most remarkable heritage sites that are valued globally are located in the Amhara region. Our organization will work to enhance the value of these resources through study and research; to provide infrastructure to undeveloped areas; to promote remote attractions, thereby increasing tourism revenue; and to ensure the primary benefit of the people.

## 3.3 Social Programs

### 3.3.1 Education

Education is a key to development and civilization. Therefore, every citizen will have the right and freedom to education. The education system in Ethiopia has not developed a system that can turn graduates into job seekers and entrepreneurs, and as a result, many educated youth are equally jobless as uneducated youth. The long-standing education policy in Ethiopia has prevented the generation from being productive and useful for the country.

An education system that is supported by science and technology, promotes competitiveness, and ensures quality will be established. Private investors who meet the criteria of the education system will be

ስለሆነም በሳይንስ እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ተወዳዳሪነትን የሚያመጣና ጥራቱን የጠበቀ የትምህርት ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል። የትምህርት ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ መመዘኛውን ለሚያሟሉ የግል ባለሃብቶች በትምህርት ኢንቨስትመንት ላይ እንዲሰማሩ ይደረጋል።

ሥርዓተ ትምህርቱ ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ተላቆ በሙያው ባለቤቶች ብቻ እንዲመራ ይደረጋል። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋና በብሔራዊ ቋንቋ እንዲሰጥ ይደረጋል። ልዩ ተሰጥዖ ያላቸውንና የላቀ ውጤት የሚያስመዘግቡ ተማሪዎችን የሚያበረታታ የልዩ ድጋፍ አሠራር ይዘረጋል፤ ከፍ ሲልም ደረጃቸውን የጠበቁ ዘመናዊ አዳሪ ትምህርት ቤቶች ፍትሓዊ በሆነ መልኩ ይገነባሉ። ከዚህም በተጨማሪ የቀደምት የዕውቀትና የጥበብ ምንጭ የሆኑት የአብነት ትምህርት ቤቶችና መድረሳዎች በልዩ ትኩረት ድጋፍ ይደረግላቸዋል። የቆየ ማንነታቸውን ለቀጣይ ትውልድ ያስተላልፉ ዘንድ አቅማቸው እየተገመገመ ወደ ከፍተኛ የትምህርትና የምርምር ማዕከልነት ደረጃ ሊያድጉ የሚችሉበት አሠራር ይዘረጋል።

### 3.3.2 ጤና

ጤና የሰው ልጆች ሁሉ ሰብዓዊ መብት ነው። ስለሆነም ማንኛውም ሰው ለጤናው ምቹ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አለው። የጤናው ዘርፍ በቅድሚያ በመከላከል መርህ ላይ ያተኮረ እንዲሆን ይደረጋል። ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ድንገተኛ የሕብረተሰብ ጤና አደጋዎችንና ወረርሽኞችን መመከት የሚያስችል የጤና ሥርዓት ይገነባል። መሠረታዊ የጤና አገልግሎት ለሁሉም ማሕበራሰብ ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል። የውጭ ሀገር እንግልትንና ወጭን መቀነስ በሚያስችል መልኩ ዘመናዊ ህክምናን በሀገር ውስጥ መስጠት የሚቻልበት ዕድል እንዲኖር ዘመኑ ያፈራቸው ቴክኖሎጅዎችንና ከፍተኛ ባለሙያዎችን ያሟሉ

encouraged to engage in educational investment.

The curriculum will be free from political interference and will be led only by professionals. Primary education will be provided in the mother tongue and national language. A system will be established to encourage and support talented students who achieve high results. Furthermore, modern boarding schools that meet standards will be built fairly.

Additionally, special attention and support will be given to traditional religious schools and madrasas, which are ancient sources of knowledge and wisdom. Their capacity will be evaluated and strengthened to become centers of higher education and research, enabling them to pass on their traditional identity to future generations.

### 3.3.2 Health

Health is a human right for all people. Therefore, everyone has the right to live in a healthy environment. The health sector will primarily focus on prevention. A health system capable of preventing man-made and natural health crises and epidemics will be built. Basic health services will be accessible to all communities. To reduce foreign suffering and costs, modern medical institutions equipped with modern technology and highly skilled professionals will be established at various levels to provide healthcare within the country. Traditional and indigenous medical practices, which have been used by our communities for centuries but are not scientifically studied, will be appropriately investigated, and if found beneficial, they

የህክምና ተቋማትም በየደረጃው እንዲኖሩ ይደረጋል። በአግባቡ ያልተጠኑ ነገር ግን ማኅበረሰባችን ለዘመናት ሲጠቀምባቸው የኖሩ ልዩ ልዩ ባህላዊ ህክምናዎች በተገቢው መንገድ እንዲጠኑ በማድረግ ጠቃሚ ሆነው ሲገኙ ከዘመናዊ ህክምና ጎን ለጎን አብረው እንዲሰጡና እንዲዳብሩ ይደረጋል።

### 3.3.3 ባህል

ጠንካራ ባህላዊ እሴት ያለው ሕዝብ ለዛሬና ነገ ማንነቱ ያለው ድርሻ የጎላ መሆኑን በማመን ለባህላዊ እሴቶች፣ ወጎችና ልማዶች ልዩ ጥበቃ ይሰጣል። ቱባ ባህሎች በመጤ ባህል እንዳይበረዙና ለትውልዱ ማንነታቸውን ሳይለቁ እንዲሻገሩ ያላሰለሰ ጥረት ይደረጋል።

### 3.3.4 ሚዲያ

ሚዲያ ለአንድ ሀገር ዕድገት መሠረት ከመሆኑም በላይ ዜጎች መረጃ የሚለዋወጡበትና ድምፃቸውን የሚያሰሙበት ትልቅ ተቋም ነው። በሚዲያ ምክንያት ዓለም አንድ መንደር በሆነችበት በዚህ ዘመን ሚዲያ የተቋማትና የዜጎች የዕለት ከዕለት የሕይወት አጋር ሆኖ ይገኛል። ስለሆነም ድርጅታችን የፕሬስ፣ ኤሌክትሮኒክና ሳይበር ሚዲያው በሁሉም ዘርፍ ተደራሽ፣ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ እንዲሠራ በአዋጅ ይቋቋማል።

will be integrated and developed alongside modern medicine.

### 3.3.3 Culture

Recognizing that a strong cultural identity is vital for today and for future generations, the organization will provide special protection for cultural values, traditions, and customs. Efforts will be made to prevent traditional cultures from being distorted by foreign influences and to ensure they are passed on to future generations without losing their identity.

### 3.3.4 Media

The media is not only a foundation for development but also a crucial institution where citizens exchange information and express their voices. In the 21st century, where the world has become a global village due to media, it serves as a daily companion for institutions and citizens. Therefore, our organization will establish a special proclamation to ensure that the press, electronic, and cyber media operate accessibly, freely, and impartially in all sectors.

AMHARA FANO PEOPLE'S ORGANIZATION

# የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት (አፋሕድ)

## ፍኖተ-መርህ

**አፋሕድ**

**የአማራን ሕዝብ የኅልውና አደጋ ይቀለብሳል፣**

**ዘላቂ ሰላምና ፍትሕን ያሰፍናል!**

ድል ለአማራ ሕዝብ!
ሰላም ለኢትዮጵያ!
መስከረም፣ ፳፻፲፰ ዓ.ም.
ኢትዮጵያ

# AMHARA FANO PEOPLE'S ORGANIZATION (AFPO)

## MANIFESTO

**AFPO**

**Reverses the existential threat to the Amhara people and Establishes lasting peace and justice!**

Victory to the Amhara People!
Peace for Ethiopia!
September, 2025
Ethiopia